# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 199 መጋቢት 19 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# በግጭት ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የሚሰራጨው የሰብዓዊ ርዳታ ተጠናክሮ ቀጥሏል

## - ባለፉት ስድስት ወራት ለመቀሌ እና ሽረ 2 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ተልኳል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በግጭት ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የሚሰራጨው የሰብዓዊ ርዳታ ተጠናክሮ ቀጥሏል ሲል የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስታወቀ:: ከጥቅምት ወር ጀምሮ 2 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ወደ መቀሌ እና ሽረ እንደተላከም ተገልጿል::

የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በትግራይ፣ አማራ እና አፋር ክልሎች በግጭት ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የሚሰራጨው የሰብዓዊ ርዳታ ተጠናክሮ ቀጥሏል:: ከሰብዓዊ ድጋፉ ባሻገር በተለይ በሽረ እና መቀሌ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮችና ለአገልግሎት ማስፈጸሚያ የሚውል ጥሬ ገንዘብ ተልኳል::

አሁን ላይ በትግራይ ክልል ከ5 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ፣ በአማራ ክልል ከ2 ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ እና በአፋር ክልል ደግሞ ከ715 ሺህ በላይ በአጠቃላይ ከ8 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ እርዳታ ፈላጊ ዜጎች መኖራቸውን አቶ ደበበ ገልጸዋል::

በግጭት ሳቢያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## "የፒያኖዋ እመቤት"

### እማሆይ ጽጌማርያም ገብሩ አረፉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- "የኢትዮጵያ ረቂቅ ሙዚቃዎች እናት" በመባል የሚታወቁት እማሆይ ጽጌማርያም ገብሩ በ100 ዓመታቸው በትናትናው እለት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

"የፒያናዋ እመቤት" ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በዞኑ ከበልግ እርሻ 11 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ከበልግ የግብርና ሥራዎች ከ11 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚጠበቅ የጉራጌ ዞን ግብርና መምሪያ አስታወቀ። በበጋ መስኖ ደግሞ 14 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት መታቀዱ ተገልጿል።

የዞኑ ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ አበራ ወንድሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ የበልግ እርሻ ከ97 ሺ ሄክታር በላይ መሬትን በተለያዩ ሰብሎችና የአትክልት ዝርያዎች ለመሸፈን እየተሠራ ይገኛል።

በበልግ እርሻው እስካሁን ከ22 ሺ ሄክታር በላይ መሬት በሰብል ተሸፍኗል ያሉት መምሪያ ኃላፊው፤ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ቦሎቄ ፣ሰሊጥ እንዲሁም ስኳር ድንችና



በዞኑ ከበልግ እርሻ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN COMMUNICATIONS AUTHORITY

የሚሰጡ አገልግሎቶች
- ለቴሌኮም እና የፖስታ አገልግሎት አቅራቢዎች ፈቃድ መስጠት
- የቴሌኮም እና የፖስታ አገልግሎቶችን መቆጣጠር
- የፍሪኩዌንሲ እና የቴሌኮም ቁጥር ሀብቶችን ማስተዳደር
- የቴሌኮም መሳሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጥ
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቅሬታ መፍታትና መብት ማስጠበቅ
- የዘርፉን ፍትሃዊ ተወዳዳሪነት ማበረታታት
- ሁሉን አቀፍ የቴሌኮም አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ታሪፍ መቆጣጠር

አድራሻ ከኤድናሞል ወረድ ብሎ ሮቤል ፕላዛ ህንፃ
+251-11-692-80-42 | contact@eca.et
9991 | https://www.eca.et

ጥራት ያለው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ እንጥራለን!


## ለ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከአንድ ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች እንደሚመዘገቡ ይጠበቃል

### - ምዝገባው ከነገ ጀምሮ ይካሄዳል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የ2015ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ለመውሰድ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ይመዘገባሉ ተብሎ ይጠበቃል ሲል የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት አስታወቀ። አገልግሎቱ የተፈታኞችን ምዝገባ አፈጻጸም ሂደት አስመልክቶ በትናንትናው ዕለት መግለጫ ሰጥቷል።

የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር እሸቱ ከበደ ትናንት በጽሕፈት ቤታቸው በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ከምዝገባው ቀን በኋላ የሚመጡ ማናቸውም የስህተት ማስተካከያ ጥያቄዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

ለ12ኛ ክፍል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ዜና


ሌንሳ መኮንን

# አዲስ አበባ ከተማን አዲስ ገጽታ የሚያላብሱ ዲዛይኖች ሥራ ሊጀምሩ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባሕላዊ ጠቀሜታዋ የጎላ እንዲሆን አዲስ ገጽታን የሚያላብሱ ዲዛይኖች ወደ ሥራ ሊገቡ መሆኑን የፌዴራል መሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡

የፌዴራል መሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን «ለሸገር አዲስ ገጽታ» በሚል ተነሳሽነት የዲዛይን ጽንሰ ሀሳብ ውድድር ቀርጾ የሽልማትና እውቅና ሥነሥርዓት በትናንትናው ዕለት አካሂዷል፡፡

በሽልማትና እውቅና ሥነሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የፌዴራል መሬት ባንክና ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር ሌንሳ መኮንን እንደገለጹት፤ ለኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ አመቺና ምቹ ለማድረግ የመጀመሪያ አካል የሆነውን የአርክቴክቶችን ልየታ ጨርሰናል ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ይዞታዎች አሉ፤ በጊዜያቸው የለሙ የነበሩ፤ ነገር ግን አሁን ላለንበት ዘመን የማይመጥኑ ይዞታዎች ለከተማው ነዋሪዎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ እነዚህን ይዞታዎች ለማልማት በዘርፉ እውቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን ተወዳድረው ጥሩ ሀሳብ ያላቸው መመረጣቸውን ጠቁመዋል፡፡ መዲናችን ለነዋሪዎቿ ምቹና ለእይታ ሳቢ እንድትሆን እንዲሁም የውጭ ጎብኝዎችን እንድትስብ ትልቅ እገዛ እንደሚኖረውም ገልጸዋል፡፡

አሸናፊዎች ያመጧቸው የዲዛይን ሀሳቦች ከከተማው ፕላን ጋር የተናበቡ ናቸው ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ጥሩ ሀሳብ አምጥተው የተሸለሙት አርክቴክቶች ሀሳባቸውን ለሕዝብ ክፍት በማድረግ አስተያየት ተሰጥቶበታል ብለዋል፡፡

በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎችም ሙያዊ አስተያየት እንደሰጡበት ተናግረውም፤ ለወድድሩ 11 ድርጅቶች ቢቀርቡም የሚፈለገውን አሟልተው የተገኙት ሁለት መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በቀጣይ የቀረቡት ሀሳቦች ወደ ዲዛይን ይቀየራሉ፤ እንዲሁም ወደሚተገበር ፕሮጀክት ይቀየራሉ ብለዋል፡፡

አኩፓንቸሪንግ አዲስ (acupuncturing Addis) ግሩፕ አባል የሆነው አርክቴክት ፍጹም አበራ በበኩሉ፤ የአዲስ አበባን ገጽታ ለመቀየር የሚያስችል ሀሳብ ይዘን በመምጣታችን አሸናፊ ሁነናል፡፡ ከመስቀል አደባባይ እስከ እንጦጦ ያለውን በመሬት ባንክ አስተዳደር የሚገኙ የመሬት ይዞታዎችን ለከተማዋ በኢኮኖሚያዊ፣ በማኅበራዊና በባሕል ለከተማዋ ነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው እንዲሆኑ የሚያስችል ሀሳቦችን ይዘን መጥተናል፡፡ በቅርቡም ወደ ተግባር እንገባለን ብለዋል፡፡

በቀጣይ የዲዛይኑን ሀሳብ ወደ ተግባር በማውረድ አዲስ አበባን ይበልጥ የቱሪስት መናገሻ እንድትሆን ይደረጋል ያሉት አርክቴክቱ፤ በተሰጡን ይዞታዎች ውስጥ አዲስ አበባን ሊያነቃቁ የሚችሉ ተጨማሪ የመዝናኛ ስፍራዎች ሊይዙ የሚችሉ ሀሳቦችን እንተገብራለን ሲሉ ገልጸዋል፡፡ አዳዲስ ዲዛይኖችን በመሥራት አዲስ አበባ ለነዋሪዎቿና ለጎብኚዎቿ ምቹ ከተማ እንድትሆን ለማድረግ እንደሚሠሩም ገልጸዋል፡፡

# በወረዳው ከሦስት ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለምቷል

- 120 ሺህ ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በበጋ መስኖ እርሻ ከሦስት ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በስንዴ መልማቱን የሰሜን ወሎ ዞን ራያ ቆቦ ወረዳ ግብርና ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡ ከለማው እርሻ 120 ሺህ ኩንታል የስንዴ ምርት ይጠበቃል፡፡

በአማራ ክልል፣ ሰሜን ወሎ ዞን፣ የራያ ቆቦ ወረዳ ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዳኜ ደሳለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በወረዳው ከለማው አራት ሺህ 502 ሄክታር መሬት መካከል ሦስት ሺህ አራት በላይ መሬት በስንዴ የተሸፈነ ሲሆን ቀሪው አንድ ሺህ 497 ሄክታር መሬት በቅመማ ቅመም፣ በጥራጥሬ፣ በአትክልትና ቋሚ ፍራፍሬ ተሸፍኗል፡፡

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ የተከናወነው በ29 ቀበሌዎች በ187 ክላስተር ሲሆን 11 ሺህ 900 የሚሆኑ አርሶ አደሮች በልማቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ እንዲሁም በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ሰባት ሺህ 200 አርሶ አደሮች ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉ የወረዳው ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ገልጸዋል፡፡



የስንዴ ልማቱ ማስጀመሪያ ፕሮግራም የተካሄደባቸው አራዱም፣ አሚድ እና አቧሬ ቀበሌዎች ላይ ምርት የመሰብሰብ ሥራ የተጀመረ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ምርት የመሰብሰብ ሥራው ከአንድ ወር በኋላ ይጠናቀቃል ብለዋል፡፡

በወረዳው አርሶ አደሮቹ ልማዳዊ ከሆነ አስተራረስ ወጥተው ዘመናዊ አስተራረስን እንዲከተሉ እና አዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም እንዲችሉ በወረዳው እና ቀበሌ ግብርና ባለሙያዎች በተቀናጀ ሁኔታ ሥልጠና እንደተሰጣቸው አስታውቀዋል፡፡

በተሰጠው ሥልጠናም አርሶ አደሮቹ ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴን በመከተል፣ አዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ፣ ምርጥ ዘር በመጠቀም፣ ማዳበሪያ እና የእርሻ ሜካናይዜሽን ከመጠቀም አንጻር አፈጻጸሙ የተሻለ ነው ብለዋል፡፡

በወረዳው የስንዴ ምርት ያልተለመደ መሆኑን ያስታወሱት ኃላፊው፤ ባለፈው ዓመት በ150 ሄክታር ሦስት ቀበሌዎች ላይ ሙከራ ተደርጎ የተገኘው ውጤት አበረታች በመሆኑ በዘንድሮው ዓመት 29 ቀበሌዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

በወረዳው አጠቃላይ ከለማው የበጋ መስና ስንዴ 120 ሺህ ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ የወረዳው ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተናግረዋል፡፡

በአማራ ክልል፣ ሰሜን ወሎ ዞን የሚገኘው የራያ ቆቦ ወረዳ ባለፉት ሁለት ዓመታት በነበረው የሰሜኑ ክፍል የሀገሪቱ ጦርነት ከልማት ተስተጓጉሎ መቆየቱ የሚታወስ ነው፡፡

# ድጋፉ በኦሮሚያ ያለውን የንጹሕ መጠጥ ውሃ ሽፋንና የጤና ሁኔታ ያሻሽላል

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በጃፓን መንግሥት የተደረገው ድጋፍ በኦሮሚያ ክልል ያለውን የጤና ሁኔታ እና የንፁሕ መጠጥ ውሃ ሽፋን እንደሚያሻሽል የገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የጃፓን መንግሥት ኢትዮጵያ የተለያዩ ሦስት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ እንዲሆን ከአንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ባደረጉበት ወቅት ድጋፉን የተቀበሉት የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰመሪታ ሰዋሰው እንደተናገሩት፤ በጃፓን መንግሥት ለኦሮሚያ ክልል የውሀ ፕሮጀክቶች ማሻሻያ የተደረገው የአንድ ቢሊዮን ብር በላይ የገንዘብ ድጋፍ በክልሉ ያለውን የጤና ሁኔታ እና የንፁሕ መጠጥ ውሃ ሽፋን ያሻሽላል።

የአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ የተደረገለት የኦሮሚያ ክልል የንፁሕ ውሀ አቅርቦት ፕሮጀክት ውሃ ወለድ በሽታዎችን በመቀነስ እና የንፁሕ መጠጥ ውሃ ሽፋን በማሻሻል በክልሉ ያለውን የጤና ሁኔታ ያሻሽላል ብለዋል።

የውሃ ፕሮጀክቱ ዓላማ በኦሮሚያ ክልል በምሥራቅ ሸዋ እና አርሲ ዞኖች ስድስት ከተሞች ላይ የቧንቧ ውሃ አቅርቦት ተቋማትን በመትከል የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ማሻሻል ነው፡፡ ይኸውም አቅርቦት የውሃ ወለድ በሽታዎችን በመቀነስና የንፁሕ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ተደራሽነትን በማስፋት በከተማዋ የሚገኙትን የማኅበረሰብ ክፍሎች ኑሮ ለማሻሻል የበኩሉን አስተዋፅዖ ያደርጋል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ኢቶ ታካኮ በበኩላቸው፤ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ትናንሽ ከተሞች የውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ የድጋፍ ውል መፈራረማቸውን ተናግረው፤ አብዛኞዎቹ የተጠቀሱት ከተሞች በቂ የውሃ አቅርቦት አገልግሎት ሽፋን ስለሌላቸው የንፁሕ ውሃ አቅርቦት ውስንነት መኖሩ ችግር እንደሚፈጥር አብራርተዋል፡፡

ይህም ተላላፊ በሽታዎችን እና ሌሎች የንፅሕና አጠባበቅ ችግሮችን የመቀስቀስ ዕድልን እንደሚፈጥር ጠቁመው ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የንፁሕ መጠጥ ውሃ ሽፋንን ከማሳደግ በተጨማሪ በአካባቢው ያለውን የጤና ሁኔታ እንደሚያሻሽል ገልጸዋል፡፡

እንደ አምባሳደሯ ገለጻ፤ የድጋፍ ፕሮጀክቶቹ ኢትዮጵያውያንን የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ ለመላ ሀገሪቱ ሕዝቦች ጤና እና ደህንነት እንዲያመጡ ታልመው የተለገሱ ናቸው፡፡

የጃፓንና የኢትዮጵያ መንግሥታት እና ሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክሩ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

የሚደረገው የውሃ አቅርቦት ማሻሻያ በኦሮሚያ ክልል 47 ሺህ የሚጠጉ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል ሲሉም በኢትዮጵያ የጃፓን አምባሳደር ኢቶ ታካኮ ተናግረዋል ።


የጃፓን መንግሥትና ኢትዮጵያ የድጋፍ ስምምነት አድርገዋል

# ጾም ከሃይማኖታዊ ፋይዳው ባሻገር ለጤናም ወሳኝ ነው

**መስከረም ሰይፉ**



አዲስ አበባ፡- ጾም ከሃይማኖታዊ ፋይዳው ባሻገር እንደ ስኳርና ደምግፊት ያሉ በሽታዎችን በመከላከል በርካታ የጤና ጥቅሞች እንዳሉት የሥነ ምግብ መምህሩ ተናገሩ።

በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ የሥነ ምግብ መምህሩ አቶ ሀብታሙ መኩሪያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት ፤ ጾም ከሃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር በርካታ የጤና በረከቶች ያስገኛል። አንድ ሰው በሚጾምበት ወይም ምግብ ሳይበላ በሚቆይበት ጊዜ ሰውነቱ ያከማቸውን ጉልበት መጠቀም ይጀምራል። ይህም የስኳር መጠን ወይም ካሎሪንን በመቀነስ የስኳር በሽታንና ከመጠን በላይ ውፍረት ሳቢያ የሚከሰቱ በሽታዎችን ለመከላከል ይረዳል።

የተስተካከለ የምግብ ሥርዓትን አለመከተል በርካታ የጤና ጉዳቶች አሉት ያሉት መምህሩ፤ እንደ ስኳር፣ ደምግፊት፣ የልብ ሕመም እና ከመጠን በላይ ውፍረት ከሚጠቀሱት መሐከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ለእነዚህ በሽታዎች ዋነኛው ምክንያት ደግሞ ክብደት መጨመር መሆኑን ተናግረዋል።

ክብደት የሚጨምረው ሰውነት ከሚፈልገው በላይ ምግብ ሲያገኝ ወደ ሴሎች ሳይሄድ ለበርካታ ጊዜ በሰውነታችን ውስጥ ተከማችቶ ይቀመጣል። ይህም ለጤና ጠንቅ የሆነ የስብ ክምችት እንደሚፈጥር አስረድተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ጾም ከማሰብ ችሎታ ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት እንዳለው አቶ ሀብታሙ አመልክተው፤ ሰው ለተወሰኑ ሰዓታት ያለ ምግብ በሚቆይበት ጊዜ ሰውነት ምግብ ለመፍጨት የሚያውለን አቅም በመቆጠብ እረፍት ያገኛል። ይህም በምግብ መፍጨት ሂደት የሚመጣ ጭንቀትን ይቀንሳል። ጭንቀትን ተከትሎ በርካታ የአስተሳሰብ ለውጦች የሚከተሉ ሲሆን ጾምን በመጾም ጭንቀትን መቀነስ እንደሚቻልም አብራርተዋል።

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለጻ፤ ጾም በሰውነት ላይ የሚጋጥሙ እብጠቶችን በመከላከል ከፍተኛ ጥቅም አለው። በአብዛኛው ጊዜ በደም ሴል ውስጥ ሞኖሳይድ የሚባሉ በሰውነት ውስጥ የማያስፈልጉ ሴሎች የሚፈጠሩ ሲሆን እነዚህ ሴሎች በሰውነት ላይ እብጠት እንዲፈጠር ያደርጋሉ። ሰውነት ለረጅም ሰዓት ከምግብ በሚርቅበት ጊዜም በሰውነት ውስጥ አላስፈላጊ ሴሎች እንዳይፈጠሩና ቢፈጠሩም ጉዳት እንዳያደርሱ ይረዳል።


እነዚህ ሴሎች የሰውነት መቆጣትና እብጠት የሚያስከትሉ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህም ለደም መርጋት እና ለካንሰርን በሽታ ያጋልጣል። ጾም ከሃይማኖታዊ ፋይዳው በተጨማሪም እነዚህ ጥቅሞች ስለሚኖሩት አልፎ አልፎ ከምግብ መራቅ ይመከራል ብለዋል።

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለጻ፤ በሳይንሱ ዓለም ጤናማ የሚባለው ጾም አልፎ አልፎ የሚጾመው ሲሆን ውጤታማ ነው የሚባለው የጾም አይነትም ከ 16 እስከ 24 ሰዓት የሚቆየው ነው። ይህም የተሻለ የጤና ጥቅም ያስገኛል።

# 166 የውሀ ሞተር ፓምፖች ለአርሶአደሮች ተሰራጩ

## - 20 ትራክተሮች በቅርቡ ይሰራጫሉ

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- የእርሻ ስራን ሜካናይዝድ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በድጎማ የተገኙ 166 የውሀ ሞተር ፓምፖች ለአርሶ አደሮች መሰራጨታቸውን በሰሜን ወሎ ዞን የራያ ቆቦ ወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት አስታወቀ። የክልሉ መንግስት 20 ትራክተሮችን በቅርብ ቀን ለወረዳው አርሶ አደሮች እንደሚያሰራጭም ተጠቁሟል።

የራያ ቆቦ ወረዳ አስተዳዳሪ አቶ ሞላ ደሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በወረዳው የሚገኙ አርሶ አደሮች የእርሻ ሜካናይዜሽን እንዲጠቀሙ በማድረግ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በትኩረት እየተሰራ ይገኛል።

ከአማራ ክልል ግብርና ቢሮ በድጎማ የተገኙ 166 የሞተር ፓምፖች ለአርሶ አደሮች፣ በማህበር ተደራጅተው ለሚያለሙ ወጣቶች እና በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ሞተራቸው ለወደመባቸው አርሶ አደሮች የማሰራጨት ስራ ተሰርቷል ብለዋል።

በአንድ ሞተር ፓምፕ እስከ አምስት ሄክታር ማልማት ይቻላል ያሉት አስተዳዳሪው፤ በሁሉም ፓምፖች የማልማት ስራ እየተከናወነ ሲሆን፤ ምርትና ምርታማነት እንዲጨመር ለማድረግ ሚናቸው የጎላ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በወረዳው በትራክተር የሚታረስ ሰፊ መሬት ከመኖሩ የተነሳ ፍላጎት ያላቸው አርሶ አደሮች የትራክተሩን ዋጋ 20 በመቶ ቆጥበው ትራክተር እንዲያገኙ የክልሉ መንግስት አመቻችቷል። በዚህም መሰረት በቅርብ ቀን 20 አርሶ አደሮች ትራክተር ማግኘት እንደሚችሉ አስታውቀዋል።

በተጨማሪም በወረዳው 33 የመስኖ ካናሎች እንዳሉ ያስታወሱት አስተዳዳሪው፤ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት 12ቱ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል። አሁን ላይ አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግና በፍጥነት ወደ ስራ ለማስገባት ጥገና እየተደረገላቸው እንደሚገኝ አብራርተዋል።

በወረዳው የለማው የበጋ እርሻ ስራ 17 ትራክተሮችን በመጠቀም ሲሆን፤ የተገኘው ውጤት አበረታች ከመሆኑ የተነሳ በቀጣይ የሚለሙ ማንኛውም አይነት የእርሻ ስራዎችን ሜካናይዝድ ለማድረግ በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል።

ለእርሻ ስራ የሚውሉ ግብዓቶችን ምርጥ ዘር እና ማዳበሪያን ከመጠቀም አንጻርም አርሶ አደሮቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት እና መሻሻል እንዳለ ገልጸዋል። እንዲሁም ከተበጣጠሰ የአስተራረስ ዘዴ ወጥተው በክላስተር እየተጠቀሙ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

አርሶ አደሮቹ ልማዳዊ ከሆነ አስተራረስ ወጥተው ሳይንሳዊ አስተራረስንና አዲስ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ከቻሉ የአካባቢውን ምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ አልፈው ምርታቸውን ለውጪ ገበያ ማቅረብ ይችላሉ ብለዋል።

ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ከተቻለ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈ በግብርናው ዘርፍ አበረታች ውጤት ማምጣት ይቻላል ብለዋል።

# በመዲናዋ ከ681 ሚሊዮን ብር በላይ ንብረት በእሳት አደጋ ወድሟል

## - ከሰባት ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት ማዳን ተችሏል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ባለፉት ስምንት ወራት በደረሰ የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ከ681 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት መውደሙን የከተማዋ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ። ከሰባት ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት ከእሳትና ድንገተኛ አደጋ ማዳን መቻሉንም አስታውቋል።

የአዲስ አበባ የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ንጋቱ ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ባለፉት ስምንት ወራት በተለያዩ ቦታዎችና በኦሮሚያ ልዩ ዞን ከተሞች በደረሰ የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ከ681 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት ወድሟል። አደጋውን ለመከላከል በተሠራው ሥራም ከሰባት ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት ማዳን ተችሏል።

በመዲናዋ ባለፉት ስምንት ወራት የደረሱ የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች በተለያየ መንስኤ ነው ያሉት አቶ ንጋቱ፤ አብዛኛዎቹ አደጋዎች የተከሰቱት በኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ በሚፈጠር ግንኙነት እና በምግብ ማብሰል ጊዜ በሚፈጠር የጥንቃቄ ጉድለት መሆኑን ተናግረዋል።

በተያዘው ዓመት ስምንት ወራት የነበረው የእሳትና አደጋ ክስተት ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በመዲናዋ የደረሰው የእሳት አደጋና የንብረት መውድም መጨመሩን አብራርተዋል።

የአዲስ አበባ የእሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ዋና ሥራው አደጋን መቀነስና መቆጣጠር ነው ያሉት አቶ ንጋቱ፤ ተቋሙ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አደጋዎች ከመከሰታቸው በፊት የቅድመ መከላከልና ከተከሰቱም በኋላ የመከላከልና የማዳን ሥራ እየሠራ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

በመዲናዋ የሚደርሰውን የእሳትና ድንገተኛ አደጋን ከመድረሱ በፊት ለመከላከል ኅብረተሰቡ የቅድመ መከላከል ሥራ መሥራት እንደሚገባ ጠቁመው ከሚዲያ የሚተላለፉ መልዕክቶችን በመከታተል ሊተገብር ይገባል ብለዋል።

የእሳት እና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በሚሰጠው አገልግሎት ብቻ በመዲናዋ የሚደርስውን አደጋና የሚወድመውን ንብረት ሙሉ በሙሉ ለመከላከል አዳጋች ስለሚሆንበት ማኅበረሰቡ ከተቋሙ ጋር በትብብር መሥራት ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

በየጊዜው የሚደርሰውን የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ለመቀነስ ኮሚሽን መሥሪያ ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ መሆኑን ጠቁመው ኅብረተሰቡ ለአደጋ የሚያጋልጡ ማናቸውንም ክስተቶች በንቃት መከታተል ይኖርበታል ሲሉ አሳስበዋል።

ማኅበረሰቡ ለእሳትና ለተለያዩ አደጋዎች የሚያጋልጡ ነገሮች ትኩረት ሰጥቶ በመከታተል የቅድመ ጥንቃቄ ሥራ በመሥራት አካባቢውን ከአደጋ በመከላከል የሚወድመውን ሀብትና ንብረት ሊያድን ይገባል ብለዋል።

# በከተማዋ የ"ኢ-ስኩል" መተግበሪያ ተግባራዊ ሊደረግ ነው

ሳሙዔል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል 200 ሚሊዮን ብር በሚጠጋ በጀት በ55 ትምህርት ቤቶች የኢ-ስኩል መተግበሪያ ተግባራዊ ሊያደርግ መሆኑን የመዲናዋ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ የትምህርት ቴክኖሎጂና መረጃ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ደረጄ ዳኜ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ "ኢ-ስኩል" ትምህርት ቤቶች የሚሠሩትን አጠቃላይ ሥራ በዘመናዊ መንገድ እንዲሠሩ የሚያደርግ መተግበሪያ ነው።

ከዚህ ቀደም ሕፃናት በክፍላቸው ደረጃ ማወቅ የሚጠበቅባቸውን ዕውቀትና ክህሎት የሚያስጨብጥ አሠራር ባለመኖሩ እንደሀገር ከፍተኛ ችግር መፍጠሩን ያነሱት አቶ ደረጄ፤ በ2016 ዓመተ ምሕረት ተግባራዊ የሚደረገው የ"ኢ-ስኩል" ሥርዓት ችግሩን በመቅረፍ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ጉልህ ሚና አለው ብለዋል።

ኢ-ስኩል በውስጡ የትምህርት ቤት መረጃ ማኔጅመንት ሥርዓት ያለው ሲሆን ይህም በትምህርት ቤቶች ያለው አጠቃላይ መረጃ የሚመዘገብበት መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይ ዓመት የትምህርት ቤት መረጃ ማኔጅመንት ሥርዓትን በ55 ትምህርት ቤቶች ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ዕቅድ ይዟል ብለዋል።

የ"ኢ - ስኩል" መተግበሪያ በውስጡ የትምህርት ቤት መረጃ ማኔጅመንት፣ ዲጂታል ቤተ መጽሐፍት፣ ለርኒግ ማኔጅመንት፣ የትምህርት ቤት ፖርታል እና ቢዝነስ ኢንተለጀንስ የሚባሉ ሥርዓት ያለው ነው። ተማሪዎች የሚፈልጓቸውን መጽሐፍት ባሉበት ሆነው እንዲያገኙ የሚያስችል፤ በራሳቸው መማር እንዲችሉ የሚያደርግ፤ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች የሚያገናኝ እና ሰው ሠራሽ ክህሎት ባለው መልኩ መረጃዎችን የሚያሳውቅ ሥርዓት እንደሆነም አቶ ደረጄ አብራርተዋል።

መተግበሪያውን በ55 ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ ለማድረግ ዕቅድ ተይዟል ያሉት አቶ ደረጄ፤ የቴክኖሎጂውን አጠቃቀም በሚመለከት ለ55ቱ ርዕሰ መምህራን ስልጠና በተለያዩ ጊዜያት ተሰጥቷል። ይህም የተደረገው ሁሉንም መምህራን በአንድ ጊዜ ተደራሽ ማድረግ ስለማይቻል ነው ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ "ኢ - ስኩል" ወላጆች ልጆቻቸው በትምህርት ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ በቀላሉ እንዲያውቁ ያደርጋል። ተማሪዎች ደግሞ የሚፈልጉትን መረጃ ባሉበት ሆነው እንዲያገኙ የሚያደርግ ሲሆን መምህራንም ተማሪዎች በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ ይረዳቸዋል ብለዋል።

ይህ መሆኑ የተማሪዎችን ዕውቀትና ክህሎት ለማሻሻል እንደሚረዳ የተናገሩት አቶ ደረጄ፤ ተማሪዎች መተግበሪያውን በሚገባ እንዲጠቀሙ የአይ ሲ ቲ ቤተ ሙከራ እና የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ተመቻችቷል ብለዋል።

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

# በዞኑ ከበልግ እርሻ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ድንች በበልግ እርሻው እየለሙ ከሚገኙ ምርቶች መካከል መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ በዞኑ ከበልግ ግብርና ከሚጠበቀው ከ11 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ውስጥ ከ7 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታሉ ምርት በአትክልት ዘርፍ ሲሆን፣ ቀሪው ደግሞ በአዝርዕት ዘርፍ የሚለማ መሆኑን አስታውቀዋል።

በበልግ ግብርናው ከሚለማው መሬት 17 ሺህ ሄክታሩ ላይ ድንች እየተመረተ መሆኑን የተናገሩት ኃላፊው፤ በዞኑ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጫ በስፋት እየተሠራባቸው ከሚገኙ ምርቶች መካከል ድንች ዋነኛው መሆኑን ገልጸዋል።

ከበልግ ግብርና ባለፈ በዞኑ በበጋ መስኖ ከ53 ሺህ 213 ሄክታር መሬት በላይ በአዝርዕትና በአትክልት ሰብሎች ተሸፍኗል። በዚህም ከ 14 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል ብለዋል።

በበጋ መስኖ በዘር ከተሸፈነው መሬት ውስጥ 1 መቶ 34 ሺህ ኩንታል በላዩ የስንዴ ምርት የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪ ከበጋ መስኖ የአትክልት ልማት 14 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል ሲሉ አስታውቀዋል።

በዞኑ የበጋ መስኖ ሥራው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን የተናገሩት ኃላፊው፤ በውስን ቀበሌዎች የተጀመረው የበጋ መስኖ ስንዴ በበጀት ዓመቱ ሰፋ ባለ መንገድ 191 ቀበሌዎች ላይ ተግባራዊ መደረጉን ገልጸዋል።

የበጋ መስኖ ሥራው የአርሶ አደሮች ተጠቃሚነት በማሳደግና ለወጣቶች የሥራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ በጎ ሚና እየፈጠረ ይገኛል ሲሉ አቶ አበራ ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ ከበልግና ከበጋ መስኖ የታቀደውን ምርት ለማግኘት ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ እስከ እንክብካቤውና ድህረ ምርት ድረስ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ኃላፊው እንደገለጹት፤ ለእርሻ ሥራዎቹ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የግብርና ግብዓቶች ቀርበዋል። የተለያዩ የዕፅዋት በሽታ መከላከያ ዘዴዎችን ለአርሶ አደሮች የማስተዋወቅ ሥራ ተከናውኗል።

የአካባቢው የአየር ፀባይ በመለየት በተለይ ከአትክልት ምርት ጋር ተያይዞ ለየአካባቢው የሚሆን የምርጥ ዘር ዓይነቶችን በማቅረብ እንዲሁም ከስንዴ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ዋግና የተለያዩ በሽታዎች በምርታማነቱ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ቀድሞ የመከላከል ሥራ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

# በግጭት ሳቢያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ አቶ ደበበ ገለጻ፤ ለእነዚህ ዜጎች በመጀመሪያ ዙር 141 ሺህ 671 ሜትሪክ ቶን በላይ የሰብዓዊ እርዳታ ምግብ የተሰራጨ ሲሆን፤ የ2ኛውን ዙር ጨምሮም እስካሁን ለሶስቱ ክልሎች 282 ሺህ 934 ሜትሪክ ቶን የሰብዓዊ እርዳታ ምግብ በየብስና በአውሮፕላን ማሰራጨት ተችሏል::

መንግስት 15 ሺህ 666 ሜትሪክ ቶን የሰብዓዊ እርዳታ ማቅረቡን የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ ሌላው ድጋፍ በ29 አጋር ድርጅቶች በኩል የተደረገ መሆኑን አስረድተዋል::

በግጭት ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የሚሰራጨው የሰብዓዊ እርዳታ ተጠናክሮ መቀጠሉን በመጥቀስ፤ በተለይም ተጋላጭ ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ለእናቶች፣ ሕጻናት፣ ነፍሰጡር እናቶች እና አዛውንቶች ደግሞ 5 ሺህ 938 ሜትሪክ ቶን አልሚ ምግብ ተደራሽ መሆኑን አብራርተዋል::

ከጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም እስካሁን ባለው ጊዜ ለሥራ ማስኬጃና አስተዳደራዊ ጉዳዮች የሚውል 2 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ወደ መቀሌ እና ሽሬ መላኩንም ዳይሬክተሩ ገልጸዋል:: ለዚህም 119 ድርጅቶች ድጋፍ ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል::

# “የፒያኖዋ እመቤት” ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በፒያኖ የሙዚቃ ሥራዎቻቸው “የፒያኖዋ እመቤት” የሚል ስያሜን ማግኘት የቻሉት የቀድሞዋ የውብዳር ገብሩ፣ የአሁኗ እማሆይ ጽጌማርያም ገብሩ እ.ኢ.አ ታኅሣሥ 4 ቀን በ1915 ዓ.ም ከአባታቸው ከከንቲባ ገብሩ ደስታ እና ከእናታቸው ወይዘሮ ካሣዬ የለምቱ ተወለዱ።

እማሆይ ጽጌማርያም ትምህርታቸውን ስዊዘርላንድ ውስጥ የተከታተሉ ሲሆን፣ የሙዚቃ መሣሪያዎቹን መጫወት የተማሩትም እዚያው ነበር። በአስራዎቹ ዕድሜያቸው መጨረሻ ላይ ወደ አገራቸው ሲመለሱም ወደ መንፈሳዊ ሕይወት በማዘንበል በ21 ዓመታቸው ምንኩስናን በመቀበል ዘመናቸውን ኖረዋል።

ከ30 ዓመታት በፊት ደግሞ ወደ እስራኤል በመሄድ ኢየሩሳሌም ውስጥ በገዳማት ውስጥ ሲኖሩ ቆይተው በ100 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ ከ150 በላይ የረቂቅ ሙዚቃ ድርሰቶችን የጻፉ፤ ሦስት አልበሞችን በሲዲ እና በሸክላ ላይ ያሳተሙ ናቸው። እማሆይ ፅጌማርያም በኢትዮጵያ ቀዳሚዋ የቫዮሊን እና ፒያኖ አቀናባሪ እንደነበሩም ይነገራል።

ከትምህርት መልስም በ19 ዓመታቸው ነበር ወደ ወሎ ግሸን ማርያም ገዳም በመሄድ በ21 ዓመታቸው ምንኩስናን የተቀበሉት። ወላጆቻቸው ያወጡላቸው ስም የውብዳር ሲሆን በወጣትነታቸው ምንኩስናን ከተቀበሉ በኋላ መጠሪያቸው ወደ እማሆይ ጽጌማርያም ተቀይሯል።

እንደ ኤፍቢሲና ኢቢሲ ዘገባ፤ እማሆይ ጽጌማርያም ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ኑሯቸውን በእየሩሳሌም አድርገዋል።

አባታቸው ገብሩ ደስታ የአዲስ አበባ ከንቲባ የነበሩ ሲሆን በአፄ ኃይለስላሴ ዘመንም የፓርላማ አፈ ጉባኤ በመሆን ማገልገላቸውን የቤተሰባቸው ታሪክ ያስረዳል።



# ለ12ኛ ክፍል መልቀቂያ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ምዝገባው የሚከናወነው በበይነ መረብ ሲሆን ፈተናው የሚሰጠው በዩኒቨርስቲዎች ይሆናል።

ፈተና የሚሰጥበት ቀንም ከምዝገባው መጠናቀቅ በኋላ የሚገለጽ ይሆናል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ባለፈው ዓመት የተፈጠረው የምዝገባና የተማሪዎች መረጃ በትክክል አለመሟላት ችግር እንዳይደገም ሁሉም ባለድርሻ አካላት መረባረብ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተፈራ ፈይሳ በበኩላቸው፤ የ2015 መልቀቂያ ፈተና የሚወስዱ ተማሪዎች ምዝገባ ከመጋቢት 20 እስከ ሚያዝያ 15 እንደሚካሄድ ገልጸዋል።

በዚህ ጊዜ ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች 850 ሺህ የሚጠጉ እንዲሁም በግል 200 ሺህ የሚጠጉ ተማሪዎች ይመዘገባሉ ተብሎ ይጠበቃል ያሉት ምክትል ዳይሬክተሩ፤ በፈተና አስተዳደር ሕግ መሠረት ትክክለኛው የተመዝጋቢዎች የቁጥር መረጃ የሚታወቀው ተፈታኝ ተማሪዎች ምዝገባውን ካጠናቀቁ በኋላ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የፈተና አፈጻጸም ሥራ አስፈጻሚ አቶ ወንደሰን እየሱስወርቅ በመግለጫው ላይ እንደተናገሩት፤ ምዝገባው ለመደበኛና ለማታ ተማሪዎች በመንግሥት መደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ ለድጋሚ ተፈታኞች እና የርቀት ትምህርት ተማሪዎች በተመረጡ የወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች አማካኝነት ብቻ የሚካሄድ ነው ብለዋል።

በተቀመጠው የምዝገባ መርሐ ግብር ባሉት ተከታታይ የሥራ ቀናት በአካል ቀርቦ ያልተመዘገበ ማንኛውም ተፈታኝ ለፈተና የማይቀመጥ መሆኑን እና ከአገልግሎት በኋላ የሚቀርብ የስም፣ የጾታ፣ የዕይታ ችግር፣ የፎቶ እና የትምህርት መስክ ስህተት ማስተካከያዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም ሲል የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት አሳስቧል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰላም ስምምነቱ እንዲጸና መስራት ከሁሉም አካላት የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው!

ከሀገራዊ ለውጡ ማግስት በተፈጠሩ ሀገራዊ እና ተቋማዊ ሪፎርሞች በርካታ ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ ርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ ይሄን ተከትሎ አስደማሚ ውጤቶች የመገኘታቸውን ያህል፤ ከለውጡ መንፈስ ጋር መራመድ ያልቻሉ ተግዳሮቶችም አልጠፉም፡፡ እነዚህ ተግዳሮቶች ደግሞ ለውጡን ከመገዳደር አልፈው በሀገር እና በሕዝብ ላይ ከፍ ያለ ችግርን የጋረጡ፤ ሲከፋም ጦርነትን የጋበዙ ነበሩ፡፡

በዚህ ረገድ ሁለት ዓመታትን የዘለቀው የሰሜኑ ጦርነት አያሌ ዜጎችን አፈናቅሏል፤ ሀብት ንብረታቸውን አውድሟል፤ አካላቸውን አጉድሏል፤ የማይተካ ሕይታቸውንም ነጥቋል፡፡ በዚህ መልኩ በዜጎች ላይ ከሚገለጸው ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነልቦናዊና ሌሎችም ጉዳቶች በዘለለ፤ ሀገርን ከፍ ያለ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ዲፕሎማሲያዊ ችግር ውስጥ አስገብቷት እንደነበርም የሚታወቅ ነው፡፡

ይሁን እንጂ መንግሥት እንደ መንግሥት ችግሩን ከጅምሩ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት እና ጦርነትን ለማስቀረት ብዙ የለፋ ከመሆኑ ባለፈ፤ የአገርን ሕልውና በማስጠበቅ ጦርነት ውስጥም ሆኖ ስለ ዜጎቹ ሰላምና ደህንነት ሲል ተደጋጋሚ የሰላም ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

መጀመሪያ ደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ላይ፤ ኋላም ኬንያ ናይሮቢ ላይ በተደረሰው የሰላም ስምምነት መሰረትም፣ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት በኩል ለስምምነቱ ተፈጻሚነት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ይሄ ተግባር አድጎም ሕወሓት “አሸባሪ” የሚለው ስም እንዲነሳለት ከመደረጉም በላይ፤ የትግራይ ክልል በጊዜያዊ አስተዳደር እንዲመራ እና የጊዜያዊ አስተዳደርን ፕሬዚዳንት በመሾም ስምምነቱን መሬት የማስያዙ ጉዞ በመልካም ደረጃ እንዲራመድ እየተደረገ ይገኛል፡፡

እነዚህ ተግባራት ጦርነት ለከረመበት አካባቢ፣ በተለይም ለትግራይ ክልልና ሕዝብ ትልቅ እፎይታንና ተስፋን የሰጡ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሕዝቡ ከግማሽ ምዕተዓመት በላይ በጦርነት ውስጥ ኖሯል፤ ልጆቹን በተደጋጋሚ ለመስዋዕትነት አቅርቧል፤ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሰረቶቹ በጦርነቶች እየተናጉበት ዛሬ ላይ ደርሷል፡፡ እናም የትግራይ ሕዝብ ከጦርነት ሳይሆን ከሰላም እንደሚያተርፍ ከማንም በላይ ይገነዘባል። አሁን የተደረሰው የሰላም ስምምነት እና የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ እየተወሰዱ ያሉ ርምጃዎችም ይሄንኑ የሕዝቡን ስሜት እና ፍላጎት እውን ለማድረግ የሚከወኑ መሆናቸውን ሁሉም ሊያውቀው የሚገባ ሃቅ ነው፡፡

በዚህ ረገድ የሕዝቡ ፍላጎት በግልጽ ታይቷል፡፡ በፌዴራሉ መንግሥት እና በሕወሓት በኩል ያለው ጥረትም ተገልጧል፡፡ ሌሎች ባለ ድርሻዎችም ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ ይሄንኑ ተከትሎ በሚያሳዩትና በሚያሰሙት አቋም እየተለየ ይገኛል፡፡ ስለ ሰላም የሚናገሩ አንደበቶች የእውነት ሰላም ፈላጊ ስለመሆን አለመሆናቸው፤ ስለ ሕዝብ ጥቅምና ደህንነት የሚደሰኩሩ ምላሶች የእውነት ይሄንን ከልባቸው ያደረሱ ስለመሆን አለመሆናቸው፤ ስለ ትግራይ ሕዝብ ጥቅምና እድገት የሚሰብኩ አንደበቶች ይሄንኑ ፈልገው የሚናገሩ ስለመሆን አለመሆናቸው፤... ለሁሉም ግልጽ እየሆነ ይገኛል፡፡

ይሄን መሰሉ ጉዳይ ጊዜና ሁኔታዎች የሚያጠሩት ቢሆንም፤ ሊዘነጋ የማይገባው ግን የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ በቀጣናው ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ታስቦ እየተተገበሩ ያሉ ስራዎች ማጠንጠኛቸው አገርና ሕዝብ መሆናቸው ነው፡፡ ምክንያቱም አገር ከፓርቲም፣ ከቡድንም በላይ ናት፤ ሕዝብም ከግል ጥቅምና ፍላጎት የላቀ ነው፡፡ ስለ ቡድን እያሰቡ፣ ስለ ግል ጥቅም እየተጨነቁ አገርና ሕዝብን እንደ ካባ ደርቦ የሚደረግ ሩጫ ካለ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ ሊሆን የሚገባው ከቡድን ፍላጎት የተሻገረ፣ ከግል ጥቅምና ምኞት የተፋታ ስለ ሀገር እና ሕዝብ ደህንነት፣ ሰላምና ከፍታ የሚገለጽ ተግባር ነው፡፡

በዚህ ረገድ አሁን በትግራይ ክልል እየተደረገ እና በፌዴራሉ መንግሥት ይሁንታ እየተሰጠው እየተጓዘ ያለው የስምምነቱ አካል የሆነው ጊዜያዊ አስተዳደር የማቋቋም ተግባር፤ በዋናነት የትግራይ ክልልን ሕዝብና አጎራባች ሕዝቦችን፤ በጠቅላላው ደግሞ መላው ኢትዮጵያውያንን ወደ ዘላቂ ሰላምና ልማታቸው ፊታቸውን እንዲያዞሩ የሚያስችል ታላቅ ርምጃ ነው፡፡ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ሀገርና ሕዝብ ይሄ እንዲሆን ትልቅ ዋጋ የከፈሉበት ውድ ነገር ነው፡፡ ይሄን ውድ ነገር ለማራከስ መሞከር፣ ይሄን የሰላም አየር ለመበከል መጣጣር ደግሞ ፈጽሞ ሊታሰብ የማይገባው ብቻ ሳይሆን በእንጭጩ ሊገታ የሚገባው ነው፡፡

የሰላም ስምምነቱ እውን መሆን አገር በብልጽግና መስመሯ ፈጥና እንድትራመድ፤ መንግሥትም ለሕዝቡ ሁለንተናዊ ደህንነትና ዕድገት በሙሉ ልብ እንዲሰራ፤ ሕዝብም ስለ ሰላሙ እውን መሆን በሕብረት እንዲቆም እድል የሚፈጥርለት ነው፡፡ በመሆኑም የሰላም ስምምነቱ በሙላት እንዲፈጸም እና ከሰላም ስምምነቱ ሕዝብ እንዲያተርፍ በቅንነት መስራት ከሁሉም የሚጠበቅ ኃላፊነት ይሆናል!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ፈተና

ዳግም መርሻ

ይህ ሰሞን የምግብ (የዳቦ) ጉዳይ ሀገራዊ አነጋጋሪነቱ ጎልቱ የወጣበት ጊዜ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት በሀገሪቷ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንዴን ኤክስፖርት ልናደርግ ነው ብሎ በይፋ ከማብሰሩ አፍታም ሳቆይ ቦረናን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተከሰተው ደርቅ ምክንያት የምግብ እህል ተረጂዎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩ፣ እንደ ስንዴና ጤፍን የመሰሉ መሰረታዊ የሰብል ምርቶች ላይ እጥረት መከሰቱና የመሸጫ ዋጋቸውም ጣሪያ መንካቱ አወዛጋቢና በርካታ ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ ሆኖ ሰንብቷል።

በርካታ የሀገር ውስጥና የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንም ስለስንዴ የተትረፈረፈ ምርት በመንግሥት አካላት የተነገረውን መሬት ላይ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማነጻጸር ሲያነሱና ሲጥሉ የሰነበቱበት ሰሞን ነበር።

ምግብ ከአየር (Oxygen) ቀጥሎ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ፍላጎቶች መካከል አንዱ እንደሆነ አንድና ሁለት የለውም። የምግብ ጉዳይ ከፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ከኢኮኖሚያዊ መስተጋብራችን ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው።

በአንድ ሀገር ፈጣን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ለማምጣትና ዘላቂ የልማት አቅም ለመገንባት ወሳኝ ነው። የምግብ ፍላጎቱና አቅርቦቱ የተሟላለት ሕዝብ ጤናማ፤ አምራች፤ ረዥም ዕድሜና አስተማማኝ የፈጠራ ብቃት ይኖረዋል። በአንጻሩ የምግብ ፍጆታው ያልተረጋገጠለትና በረሃብ ቸነፈር የሚጠቃ ሕዝብ በአእምሮና በአካል የበለጸገ አይሆንም ፤ አምራች ዜጋም ሊሆን አይችልም። ይህ ደግሞ በሀገር እድገትና ልማት ላይ የሚያስከትለው ችግር በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ የምግብ እጥረት ቀውስ ያለባቸው ሀገራት ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችና ፖለቲካዊ አለመረጋጋቶች የመጋለጣቸው ሁኔታም የተለመደ ነው።

በምግብ እራስን አለመቻል ከዚህም አልፎ ሙሉ የኢኮኖሚ ነጻነትና ብሄራዊ ክብርንም ያሳጣል። የምግብ ፍላጎታቸውን ያላሟሉና ሲረዱ የቆዩ ሀገራት ለተለያየ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች የመጋለጥ እድላቸው እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ነፃነቷን ጠብቃ የቆየችው ሀገራችን የዚህ ዕውነታ ተጋሪ ናት ።

> **በምግብ እራስን አለመቻል ከዚህም አልፎ ሙሉ የኢኮኖሚ ነጻነትና ብሄራዊ ክብርንም ያሳጣል። የምግብ ፍላጎታቸውን ያላሟሉና ሲረዱ የቆዩ ሀገራት ለተለያየ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖዎች የመጋለጥ እድላቸው እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ነፃነቷን ጠብቃ የቆየችው ሀገራችን የዚህ ዕውነታ ተጋሪ ናት**

የምግብ ዋስትና ጉዳይ ከ1970ዎቹ ጀምሮ የተያዘ ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ ነው። በ1990ዎቹ መጨረሻ ግን ከሚሊኒየሙ ግቦች የመጀመሪያው ከሆነው ረሃብን የማጥፋት ዘመቻ ጋር እንዲያያዝ ተደርጎ በመታሰቡ ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ ሀገሮች የፖሊሲዎቻቸው አካል ካደረጉት ቆይተዋል።

በዓለም የምግብ ድርጅት (FAO) ትርጓሜ መሰረት የምግብ ዋስትና (Food Security) ተረጋገጠ የሚባለው በአንድ ሀገር ያሉ ሁሉም ሰዎች ንቁና ጤናማ ሕይወት ለመኖር የሚያስፈልጓቸውን በቂ፣ ጤናማና የተመጣጠነ ንጥረ ነገር ያለው የምግብ አማራጭ ለማግኘት የሚችሉበት የኢኮኖሚ አቅምና አቅርቦት ሲኖራቸው ነው፡፡ የምግብ ዋስትና እንደምታው የራስን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የውስጥ ፍጆታን ከማሟላትም የዘለለ ነው፡፡

የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ የምርት እጥረትና የዓለም አቀፍ ገበያ ውጣ ውረድ በሚያጋጥምበት ሁኔታም ለዜጎች በቂ የምግብ ምርት ሳያስተጓጉል የሚያቀርብ የምርት፤ የግብይትና የመጠባበቂያ ክምችት ሥርዓት የመዘርጋት እንዲሁም የኢኮኖሚ አቅም ማዳበርንም ያካትታል፡፡

ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከስምንት መቶ ሚሊዮን የሚበልጥ ሕዝብ በምግብ እጥረት ችግር ወይም የምግብ ዋስትናው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ውስጥ የእንደሚገኝ የዓለም የምግብ ድርጅት (World Food Program) ሪፖርት ያመላክታል፡፡ ወደ ሁለት ቢሊዮን የሚገመት ሕዝብ ደግሞ ጠቃሚ ቫይታሚኖችንና ማዕድናትን እንደማያገኝ ይገለጻል። ይህ ሁኔታ የተደበቀ ረሃብ (የምግብ እጥረት) (hidden hunger) መከሰቻ ተብሎ ይታወቃል፡፡

በአፍሪካ ደረጃ የምግብ እጥረት የሚፈትነው ሕዝብ ቁጥር በጠቅላላው 21% ሲሆን፣ ከሰሃራ አፍሪካ በታች ከሚገኙት ውስጥ ደግሞ ከሕዝቡ 25% የሚሆነው በምግብ እጥረት ችግር እጦት የሚንገላታ መሆኑን አሃዛዊ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም 13 ነጥብ 7 በመቶ የሚሆኑ ጨቅላ ሕጻናት በተመጣጠነ ምግብ ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ሲሆን 30 ነጥብ 7 የሚሆኑ ከ 0 እስከ 5 ዓመት እድሜ ያላቸው ሕጻናት ደግሞ የቀነጨሩ መሆናቸውን የዓለም አቀፍ የተመጣጠነ ምግብ ሪፖርት ያሳያል።

አህጉረ አፍሪካ 9 ቢሊዮን የሚያክለውን የአህጉሪቱን ሕዝብ መመገብ የሚያስችል ለእርሻ ተስማሚ የሆነ መሬት ባለቤት እንደሆነች ቢነገርላትም ኢትዮጵያን ጨምሮ አብዛኞቹ ሀገሮች ይህንን ሀብት በአግባቡ ባለመጠቀማቸው ህዝቦቻቸውን ከምግብ እጥረት ፣ ከተረጂትና ከድህነት ማላቀቅና የምግብ ዋስትናን በአስተማማኝ መልኩ ማረጋገጥ ትልቅ ፈተና ሆኖባታል።

የፓን አፍሪካ ባንክ (The Pan-African bank) ያወጣው መረጃ እንደሚያሳየው፤ አህጉሪቱ ለእርሻ ተስማሚ የሆነውን 65 በመቶ የሚደርሰውን የተፈጥሮ ሀብቷን በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል ብትችል እ.አ.አ በ 2050 9 ቢሊዮን ይደርሳል ተብሎ የሚገመተውን የዓለም ሕዝብ መቀለብ የሚያስችል እምቅ አቅም እንዳላት ያትታል። ሆኖም «ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ» እንደሚሉት ብሂል ሆኖ አብዛኞቹ በአህጉሪቱ ስር የሚገኙ ሀገራት ዋና መለያቸው ረሃብ፣ የምግብ እጥረት፣ የምግብ ዋስትና ማጣትና የመሳሰሉት ክስተቶች ሆነው ዘመናትን ዘልቋል። ይህ አህጉሪቱ ጤናው የተጠበቀና አምራች ህብረተሰብ እንዳይኖራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

አህጉሪቷ የራሷን የግብርና ምርቶች በዓለም ገበያ በመሸጥ እንደሌሎቹ ሁሉ ተጠቃሚ የመሆን ሰፊ እድል ቢኖራትም፣ ዛሬም የምግብ ዋስትናዋ በከፊል የተንጠለጠለው በውጭ እርዳታና ተሸምቶ በሚገባ የምግብ እህል ላይ ነው። በዚህም ምክንያት አህጉሪቱ ካላት ውስን ጥሪት ላይ በአመት ወደ 75 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ በማውጣት ለዚሁ ዓላማ ስታውል እንደቆየች የአፍሪካ ልማት ባንክ (African Development Bank) ሪፖርት ይጠቁማል።

በኢትዮጵያም ተጨባጭ ሁኔታ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንደ ሀገር ካሉ ችግሮች መካከል አንደኛው ነው፡፡ በ 2022 ቱ የዓለም የረሃብ ምደባ መሰረት (Global Hunger Index) ኢትዮጵያ ከ 121 የዓለም ሀገራት ውስጥ 104ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠች

ወደ 6ኛ ገጽ ዞሯል

# ነፃ ሀሳብ

# የምግብ ዋስትናን ...

ከ5ኛው ገጽ የዞረ

ሲሆን በሀገሪቱ የምግብ ዋስትናቸው ያልረጋገጠ ላቸው ዜጎች ቁጥር ወደ 22.3 ሚሊዮን ይደርሳል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ሁሉም አይነት ከምግብ ጋር የተያያዙ ችግሮችን እያስተናገደች መሆኑን ይፋ አድርጓል።

ሀገሪቱ እንደ ስንዴ፣ ሩዝ፣ አተር፣ ምስር፣ ፓስታ፣ መኮረኒ... ያሉ ምርቶችን ከውጭ ለማስገባት በየአመቱ ከፍተኛ ወጪ ትከሰክሳለች። ለምሳሌ ስንዴን ከውጭ ለማስገባት በየአመቱ ከ 700 ሚሊዮን ዶላር እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር እንዲሁም ለአተር በአማካይ በየአመቱ 50 ሚሊዮን ዶላር እንደምታወጣ ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ሀገራችን ሰፊና ለም መሬት፣ ተስማሚ ሥነ ምህዳር፣ ግዙፍ የውሃ ሀብት እና በእንስሳት ሀብት የተቸረች ናት። ይሁንና ከ74 ሚሊዮን ሄክታር ሊታረስ የሚችል የመሬት ሀብቷ ያልዘመነ የአስተራረስ ዘዴን በመጠቀም እየታረሰ የሚገኘው 13 ሚሊዮን ሄክታር ብቻ ነው። ይህም በአብዛኛው ሕዝቡ ተጠጋግቶ የሚኖርባቸውን ደጋና የወይና ደጋ አካባቢዎችን አካቶ የያዘ ነው።

በእነዚህ ቦታዎች የሚካሄደው አብዛኛው የግብርና ስራም አሁንም ድረስ ኋላቀር የአስተራረስና የግብዓት አጠቃቀም ዘዴን የሙጥኝ ያለ ነው። ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ማዳበሪያ የሚጠቀመው አርሶ አደር 62 በመቶ ብቻ ነው ። እንዲሁም የምርጥ ዘር አቅርቦታችን 25 በመቶ፣ የሜካናይዜሽን አጠቃቀማችን 6 በመቶ፣ በመስመር የመዝራት ባህላችን 28 በመቶ ላይ እንደሚገኝ መረጃው ያመላክታል። በዚህ መልኩ የሚታረሰው መሬት የሚሰጠው ምርት በሄክታር አነስተኛ በመሆኑ በምግብ እራሳችንን መቻል ቀርቶ በግብርናው ዘርፍ የተሰማራውን ሰፊውን አርሶ አደር እንኳን በበቂ ሁኔታ መግቦ ማሳደር አልቻለም።

በአንፃሩ ከተሞች በአብዛኛው ሊባል በሚችል መልኩ ከገጠር በሚቀርቡ የግብርና ምርቶች ላይ ጥገኛ በመሆናቸውና የአብዛኛው ነዋሪም የኢኮኖሚ አቅም ካለው የኑሮ ውድነት አንጻር የማያወላዳ በመሆኑ የምግብ ዋስትና ችግሮችን በመሠረታዊነት ማቃለል አልተቻለም። በመሠረታዊ ምግቦች ደረጃ ሲታይ ዜጎች የሚያገኙት የካሎሪ መጠን በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

ሰፊ የከብትና የእንስሳት ሀብት ባለቤት እንደሆንን ቢነገርም "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ" እንደሚባለው ሀገራዊ ብሂል ሆኖ ሥጋ፣ ዶሮ፣ ወተት፣ ቅቤ፣ አትክልትና ፍራፍሬ... የመሳሰሉት በማእድናት የበለጸጉ ምግቦች ለአብዛኛው ዜጋ ብርቅ ወደመሆን ደረጃ ተሸጋግረዋል። የኑሮ ውድነቱና የገበያው መመሰቃቀል ደግሞ ችግሩን በይበልጥ እንዲከፋ አድርጎታል።

በአንድ ሀገር የምግብ ዋስትና ተረጋገጠ የሚባለው አብዛኛው ሕዝብ በቂ፣ ጤናማና የተመጣጠነ ምግብ በአስተማማኝ ሁኔታ ማግኘት ሲችልና በየእለቱ ከ 2,100 በላይ የካሎሪ መጠን ሲያገኝ ነው። የምግብ ዋስትና ስለመረጋገጡ ሌላው መመዘኛ ለተመጣጠነ የምግብ እጥረት የሚጋለጠው ሕዝብ ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ 5 በመቶ በታች ሲሆን ነው። በመሆኑም በእነዚህ መመዘኛዎች ሚዛን ሲፈተሽ በሀገራችን የምግብ ዋስትናን ያልተረጋገጠ ከመሆኑ ባለፈ በተለይ በገጠር የሚኖረውን ማህበረሰብ ከፍተኛ ለሆነ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት፣ ለአካልና ለአእምሮ እድገት ውስንነት (በተለይ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊ ህጻናት) ተጋላጭ እንደሆኑ ጥናቶች ያመላክታሉ።

ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ቁጥር መካከል አብላጫውን ቁጥር የሚይዘው ማህበረሰብ (80 በመቶ የሚሆነው) የኑሮው መሰረት ግብርና ነው። የሀገሪቱም አኮኖሚ በአብዛኛው ግብርናው ላይ የተንጠለጠለ ነው። ግብርና ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት 34 ነጥብ 1 በመቶ መያዙና 79 በመቶ የሚሆነው የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ገቢም ከዚሁ ዘርፍ የሚገኝ መሆኑ ነው። ያም ሆኖ ይህ ሁሉ የሰው ሃይል የተሰማራበት ግብርናችን በምግብ ራሳችንን የመቻል ፍላጎታችንን አላሳካልንም።

**ሰፊ የከብትና የእንስሳት ሀብት ባለቤት እንደሆንን ቢነገርም «ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ» እንደሚባለው ሀገራዊ ብሂል ሆኖ ሥጋ፣ ዶሮ፣ ወተት፣ ቅቤ፣ አትክልትና ፍራፍሬ... የመሳሰሉት በማእድናት የበለጸጉ ምግቦች ለአብዛኛው ዜጋ ብርቅ ወደመሆን ደረጃ ተሸጋግረዋል። የኑሮ ውድነቱና የገበያው መመሰቃቀል ደግሞ ችግሩን በይበልጥ እንዲከፋ አድርጎታል**

ለምሳሌ በእስራኤል በእርሻ የተሰማራው ሕዝብ ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ 2 ነጥብ 5 ፐርሰንት ብቻ ሲሆን ይህን ጥቂት የሰው ሀይል ይዞ የሚካሄደው ግብርና የሚካሄደው ደግሞ 20 ፐርሰንት በሆነው ለም መሬት እና 60 ፐርሰንት በሆነው ደረቅ መሬት ላይ ነው። ከዚህ አኳያ በእርሻ የተሰማራው ሕዝብ ቁጥርና የሚታረሰው የመሬት መጠን ከእኛ ጋር ሲወዳደር እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም የእርሻው ምርታማነት እራስን ከመቻል አልፎ የተትረፈረፈ የግብርና ምርት በተለይም የፍራፍሬና የአትክልት ውጤቶችን ኤክስፖርት በማድረግ በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ሀገሮች ተርታ እንድትሰለፍ አስችሏታል። በዚህም እስራኤል በአመት 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚደርስ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ታገኛለች።

እስራኤል በዓለም ላይ ከፍተኛ የወተት ምርት ከሚያመርቱ ሀገራት አንዷና ዋነኛዋ ናት። በዓመት ከአንድ የወተት ላም በአማካይ እስከ 13,000 ሊትር ወተት ታመርታለች። አብዛኞቹ ሀገራት ከአንድ ሄክታር በአማካይ እስከ 500 ኩንታል ቲማቲም የሚያመርቱ ሲሆን እስራኤል ግን በመስኖ ልማት ከአንድ ሔክታር እስከ 3000 ኩንታል ቲማቲም የምታመርትበት ደረጃ ላይ ደርሳለች ። የእኛ አማካይ ምርት ከ 350 እስከ 400 ኩንታል አይዘልም።

በሌላ በኩል በእስራኤል በምርትና በድህረ ምርት ወቅት ያለው የብክነት መጠን 0.5 በመቶ ብቻ ሲሆን የእኛ ግን ከኋላቀር አስተራረስ፣ ዘር የመዝራት፣ የአጨዳና የውቂያ የግብርና እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ከአጠቃላይ ምርታችን 25 በመቶ የሚሆነው ለብክነት ይዳረጋል።

እስራኤልን ሀገር በግብርናው ውጤታማ እንድትሆን ካደረጓት መሰረታዊ ምክንያቶች አንዱ የመስኖ እርሻን ለማካሄድ የምትጠቀመው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ነው። ለምሳሌ 62 % የሚሆነው ለመስኖ ጥቅም ላይ የሚውለው ውሃ የሚመረተው የተወገደ ውሃን መልሶ በማጣራት (waste water) እና ጨዋማ ውሃን ጨዋማ ወዳልሆነ ውሃ መልሶ በመቀየር (brackish water) ነው።

ከዚህም ባሻገር 75 በመቶ የሚሆነው የመስኖ እርሻ የሚከናወነው የጠብታ መስኖ ቴክኖሎጂን (drip irrigation) ስራ ላይ በማዋል ነው። ከዚሁ ጎን ለጎን በመላ ሀገሪቱ የሚካሄዱት ዘርፈ ብዙና ተጨባጭነት ያላቸው (applicable) የጥናትና ምርምር ተግባራት በአብይነት ይጠቀሳሉ። በእኛ በኩል ምንም እንኳን አሁን አሁን ብዙ መሻሻሎች ቢኖሩም አብዛኛው የግብርና ስራ ከሳይንሱ በጣም በራቀ ሁኔታ የሚከናወን ነው። ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማካሄድ፣ በማስተዋወቅና በማስፋት በኩልም ብዙ መንገድ ይቀረናል።

ይህ የሚያሳየን ነገር በሰው ሀብትም ሆነ በተፈጥሮ ሀብት ባለጸጋ ብንሆንም የተሰጠንን ሀብት በብቃትና በጥበብ በመጠቀም ባለመቻላችን በሚፈለገው ደረጃ ውጤት ላይ አለመድረሳችን ነው። ይህም በመሆኑ ግብርናችን የተፈጥሮ አደጋን ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋን በዘላቂነት መቋቋም እንዳንችል አድርጎናል። በአሁኑ ወቅት ቦረናን ጨምሮ በሶማሌ፣ በደቡብና ሌሎችም አካባቢዎች ከብት በቁም እስከ መሞት ያደረሰው ድርቅና ከድርቁ ጋር ተያይዞ የተከሰተው ሰብአዊ ቀውስ ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ነው።

ችግሮችን የምናነሳው ከሰራን በግብርናው ዘርፍ ያለውን መጥፎ ታሪክ መለወጥ እንደሚቻል ለማመላከት እንጂ ሂደታችን በሙሉ ጨለማ አድርጎ ለማሳየት አይደለም።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የግብርና ምርትን ለማሳደግ የማይናቅ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ከእነዚህ ጥረቶች መካከል ለማዳበሪያና ለምርጥ ዘር አቅርቦት፣ ለኩታ ገጠም እርሻ፣ ለሜካናይዜሽን አገልግሎት... ወዘተ መስፋፋት የተሰጠው ትኩረት ይጠቀሳል። ከዚህ አንጻር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በስንዴ ልማት ላይ እየታየ ያለው የምርትና ምርታማነት እመርታ ይበል የሚያሰኝ ነው። ስንዴ በመኸር ብቻ ሳይሆን በበጋ መስኖም እንዲለማ በማድረግ ውጤት ማምጣት እየተቻለ ነው።

ለምሳሌ የበጋ ስንዴ ልማት ስራዎች ከተጀመሩ ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በዘጠኙ ክልሎች በመስኖ አምራች ያልነበሩ አካባቢዎች ወደ ስንዴ ምርት እንዲገቡ ተደርጎ አመርቂ ውጤት መታየቱን የግብርና ሚኒስቴር ሪፖርት ያመላክታል። በዚህም ኢትዮጵያ በ 2015 አመት ብቻ በመስኖና በዝናብ ከ160 ሚሊዮን ኩንታል የተሻገረ የስንዴ ምርት ታገኛለች ተብሎ ይጠበቃል።

እስካሁን በመኸር ከ112 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት የተገኘ ሲሆን፣ ከበጋ የመስኖ ስንዴ ደግሞ 52 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል ነው የተባለው። ያለውን የገበያ ንረት ከማረጋጋት፣ ከምርት አቅርቦት...ወዘተ ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ችግሮች እንዳሉ ሆኖ ስንዴ በዚህ መጠን መመረት መቻሉ ለዘመናት ከረሀብተኝነት አባዜ ለመገላገል ጥረት ስታደርግ ለቆየች ሀገር ትልቅ እመርታና ሰፊ ዕድልም ይዞ የሚመጣ ነው።

ይህ መልካም ውጤት ቀጣይነት እንዲኖረው ከተሰራ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በዋና ዋና የምግብ እህሎች እራሳችንን ከመቻል አልፈን ከውጭ ድጋፍና ተመጽዋችነት ለመላቀቅ ሰፊ እድል አለን የሚል እምነት አለኝ ። ይሁንና በምግብ እራስን መቻል ብቻውን የምግብ ዋስትና ያረጋግጣል ማለት እንዳልሆነ የዘርፉ ምሁራን ደጋግመው የሚገልጹት እውነታ ነው፡፡

ምክንያቱም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ በተጓዳኝ ሌሎች በርካታ ስራዎችን መስራት የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። በሀገራችን ከሚታየው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት፣ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን፣ የአየር ንብረት ለውጥ መለዋወጥ፣ ከግብአት አቅርቦት ውስንነት...ወዘተ አንጻር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ፈተናው ቀላል እንዳልሆነ ግልጽ ነው።

ከዚህ አኳያ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሰረታዊ ነገሮች ላይ ቅድሚያ ሰጥተን መስራት እንዳለብን አምናለሁ ።

1/ በሁሉም የግብርና ዘርፎች (አይነቶች) ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ፤

2/ ለእርሻ ስራ ያልዋሉ አዳዲስ መሬቶችን ወደ ሥራ በማስገባት የተፈጥሮ ሀብታችንን በአግባቡ መጠቀም፤

3/ የምግብ ምርቶች ላይ የሚታዩትን ውስብስብ የገበያ ሥርዓቶችን በየጊዜው እየተፈተሹ መፍትሄ ማበጀት፤

4/ ከእርሻ እስከ ገበያ ድረስ ባሉት ሂደቶች ያለውን የምርት የብክነት መጠን መቀነስ ፤

5/ የግብርና ስራን በዘመናዊ ቴክኖሎጂና በሜካናይዜሽን አገልግሎት ለማስደገፍ የሚደረገውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል፤

6/ የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን ከግብርና ሥራ ጋር አቀናጅቶ መሥራት፤

7/ ከተለመደው የአመጋገብ ባህላችን ባሻገር አዳዲስ የአመጋገብ ባህሎችን ማበረታታት።

በእኔ እምነት እነዚህ መሰረታዊ ነገሮች ላይ ግዜ ሳናጠፋ መስራት እንዳለብንና አገራችንን ከተደቀነባት የምግብ ዋስትና ስጋት እንውጣ ባይ ነኝ ። ይህ ባልሆነበት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አዳጋች ነው ብዬ እሰጋለሁ።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## እንሰት መፋቅ፣ ማብሳላትና ማዘጋጀትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ

ወርቅነሽ ደምሰው



የእንሰት ተክል በሀገራችን በርካታ አካባቢዎች በስፋት ይለማል። ከተክሉ የሚመረቱት ቆጮ፣ ቡላና የመሳሰሉትም በዋና ምግብነት ይታወቃሉ። የእንሰት ተክል በደቡብ፣ በሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች እና በኦሮሚያ ክልሎች እንደሚለማ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከተክሉ የሚገኙት ቆጮና የመሳሰሉት ምግቦች ሲመረቱ የኖሩት በባህላዊ መንገድ ሲሆን፣ በማምረቱ ሥራም የሚሳተፉት ሴቶች ናቸው። ባሕላዊ የአመራረት ሂደቱ እጅግ ኋላ ቀር በመሆኑ የእናቶችን ጊዜ ያባክናል፤ ጉልበታቸውን የሚበላና አድካሚ ነው።

ይህንን የአመራረት ዘዴ በማሻሻል ዘመናዊ ዘዴን እንዲከተል ማድረግ የእነዚህን እናቶች ድካም ከማቅለልና ጊዜያቸውን ከመቆጠብ በላይ ምርታማነትንም መጨመር መሆኑን የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ መረጃ ያመለክታል። ከእንሰት ቆጮና የመሳሰሉትን በዘመናዊ ዘዴ ማምረት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በማልማት ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑን ዩኒቨርሲቲው በቅርቡ አስታውቋል። የዛሬው ሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችንም ይህንኑ አዲስ ቴክኖሎጂና ፋይዳውን የተመለከተ ነው።

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የእንሰት ፕሮጀክት አስተባባሪና ተመራማሪ ዶክተር አዲሱ ፍቃዱ እንደሚሉት፤ ዩኒቨርሲቲው የእናቶችን ድካም የሚያቃልሉ፣ ጊዜያቸውን የሚቆጥቡ አዳዲስ ቴክኖሎጂን በመሥራት ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እያደረገ ይገኛል። አዲሱ ቴክኖሎጂ ከእንሰት ቆጮና የመሳሰሉት በባሕላዊ መንገድ የሚመረቱበትን ሂደት ሙሉ ለሙሉ ያዘምናል። ቴክኖሎጂው የምግብ ጥራትን ከማሻሻል እና ከእንሰት የሚገኘውን ጥቅም ከመጨመር አንጻር ትልቅ አስተዋፅዖ ያበረክታል።

ዩኒቨርሲቲው ከሚሰጣቸው የማኅበረሰብ አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ የማኅበረሰቡን ችግሮች በመለየት ሳይንሳዊ መፍትሔ መስጠት ነው የሚሉት ዶ/ር አዲሱ፤ በዚህም ከእንሰት የሚገኙ ምርቶችን በዘመናዊ መልኩ ማምረት የሚያስችል ቴክኖሎጂ በማበልጸግ በማኅበረሰቡ ዘንድ እንዲሞከሩ በማድረግ የተሻለ የተባለው ቴክኖሎጂ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲሆን እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በዩኒቨርሲቲው ከአምስት ወይም ከስድስት ዓመት በፊት ከተለዩ ችግሮች አንዱ ከእንሰት የተለያዩ ምርቶች አመራረት፣ ማብላላት፣ የመፋቅ ሂደት እና ምግብ የማዘጋጀት ሂደት እጅግ በጣም ጉልበት የሚጠይቁ እና ጊዜ የሚፈልጉ ከመሆናቸው ባሻገር ከእንሰት የሚገኘው ምግብ ወጥ ያልሆነ፣ ጥራቱ ከቦታ ቦታ የሚለያይ መሆኑን ያመላከተ ነው ሲሉ ተመራማሪው ያብራራሉ። ቆጮው ገበያ ላይ ሲውል የተሻለ ዋጋ የማያወጣበት ሁኔታ እንዳለም ይገልጻሉ።

ለእነዚህ ችግሮች በተቀናጀ መልኩ መፍትሔ ለመስጠት ጥናቶች መካሄዳቸውንም ጠቅሰዋል። ጥናቶቹም በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ በሆኑ የሕትመት ውጤቶች ላይ ለሕትመት እንዲበቁ መደረጋቸውን ዶ/ር አዲስ ይናገራሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ለህትመት ከበቁት ቴክኖሎጂዎች ውስጥ ቃጫውን በቀላሉ የሚለይ መፋቂያ ማሽን፣ የሚያደቅ ማሽን፣ የሚጨምቅ ማሽን እና ሌሎች አዳዲስ የማብለያ ዘዴዎችን የያዙ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም እንሰት በዘመናዊ መልኩ ከተመረተ ከእንሰት የሚገኘው ምግብ ጤንነቱ የተጠበቀ ይሆናል።

ከእንሰት ከሚመረቱት ምግቦች መካከል በተለምዶ ከምናውቃቸው ከገንፎ እና ከቂጣ በተጨማሪ ውስን ምግቦች ብቻ ናቸው ያሉት ተመራማሪው፣ በቴክኖሎጂ በመጠቀም በዘመናዊ ዘዴ የእንሰት ምርቶች ሲመረቱ ግን ከተክሉ በጣም ብዙ የምግብ አይነቶችን መሥራት ይቻላል ይላሉ።

‹‹ቀደም ሲል እንሰት ቆጮ ሆኖ ተጋግሮ የሚበላ ባህላዊ ምግብ እንደሆነ ነው የሚታወቀው›› የሚሉት ዶ/ር አዲሱ ፤ ከባህላዊ ምግብነቱ ባሻገር በቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ሲመረት ደግሞ ጥራቱ በጠበቀ ሁኔታ ስለሚመረት ነጭ፣ ጥሩ መዓዛ ያለው ቆጮ ማግኘት እንደሚቻል ይጠቁማሉ። ማሽኑ ቆጮውን በቀላሉ ወደ ዱቄት እንደሚቀይረው ተናግረው፣ ከዱቄቱ ደግሞ ዳቦ፣ ኬክ፣ ኩኪስ እና የመሳሰሉትን ሌሎች ምግቦች ማምረት እንደሚቻል አስታውቀዋል።

እስካሁን በአብዛኛዎቹ ቦታዎች እንሰት የሚፋቀውና ቆጮውም የሚለየው በእንጨት ወይም በአጥንት እና በቀርከሃ መሆኑን ያመለከቱት ዶ/ር አዲሱ፤ ቆጮው እንዲብላላ የሚደረገውም በጉድጓድ በመቅበር ረጅም ሂደቶችን እንዲያልፍ በማድረግ መሆኑን ይገልጻሉ። አዲሱ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ግን ይህንን ሁሉ ድካም በማስቀረት በዘመናዊ መልኩ ለምግብነት የሚውሉ ምርቶችን ማግኘት ማስቻሉን ይጠቁማሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ በተለመደው መንገድ ሁለት እናቶች በአንድ ላይ ሆነው አንድ እንሰት ለመፋቅ ከአንድ ቀን በላይ ሊፈጅባቸው ይችላል። በአዲሱ ቴክኖሎጂ ግን እንሰት የመፋቁ ሥራ በአብዛኛው አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል። ይህም ጊዜንም ይቆጠባል፤ የምግብን ጥራትንም ያረጋግጣል። እናቶች እንሰት ለመፋቅ የሚያስፈልጋቸውን ጊዜ ይቆጥባል፤ ጉልበታቸውን ለሌላ ሥራ እንዲያውሉ ያስችላል ብለዋል።

በተመሳሳይ በሚገባ የተበላላ ቆጮ ማግኘት እንደየአካባቢው ሁኔታ የተለያየ ቢሆንም፣ በትንሹ ከሁለት ወር እስከ ስድስት ወር ጉድጓድ ውስጥ ተቀብሮ መቆየት አለበት ይላሉ። በዩኒቨርሲቲው ቤተ ሙከራ የበለጸገው እርሾ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ግን ከሰባት እስከ አስር ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በቀላሉ የተፋቀው እንሰት ተብላልቶ ለምግብነት መዋል እንደሚችል ነው ያመለከቱት።

እናቶች መጀመሪያ የተፋቀውን እንሰት በጉድጓድ ይቀብራሉ፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ከጉድጓዱ አውጥተው ያገላብጡትና መልሰው ይቀብሩታል። ከዚያም እንደገና ያወጡትና ቦታ ይቀያይራሉ። ይህ ሂደት ረጅም ጊዜ ይወስዳል፤ ጉልበት ያባክናል። አዲሱ ቴክኖሎጂ ይህንን ሂደት የሚያሳጥር በመሆኑ የበለጸገ እርሾ በመጠቀም ከአንድ ደቂቃ በኋላ ተቀላቅሎ ይገባል፤ ከዚያም በአጭር ቀን ውስጥ አውጥቶ ለምግብነት ማዋል እንደሚቻል ይገልጻሉ። ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ አሠራሮችን ከማዘመን በተጨማሪ ጊዜንና ጉልበትን በመቆጠብ የምግቡን ጥራትና ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር መሠራቱን ተናግረዋል።

እንሰት አልሚ አርሶ አደሮች ቴክኖሎጂውን ለመጠቀም እንዲችሉ ለማድረግ የመግዛት አቅምን በተመለከተም በስፋት ጥናት መካሄዱን ነው ዶ/ር አዲሱ የጠቆሙት፤ እንሰት የሚያለሙ አርሶ አደሮች እንሰቱ የሚፍቁት በዓመት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ መሆኑን ተመራማሪው ተናግረው፣ እንሰት የሚፋቅበት ጊዜ በጣም አጭር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዓመት አንድ ጊዜ ለሚደረገው የመፋቅ ፕሮግራም ቴክኖሎጂው ያስገኘውን ማሽን መግዛት አዋጭ አይደለም ይላሉ።

ለዚህም ጥናቱን መሠረት በማድረግ እንሰት ባለበት አካባቢ በየሰፈሩ ማኅበረሰብ አቀፍ የእንሰት መፋቂያና ማብላያ ማዕከላት መገንባታቸውን ይገልጻሉ። ለአብነት በዶርዜ አካባቢ በተገነባው ማዕከል ቴክኖሎጂዎቹ እንዲገቡ ተደርጎ ሥራ መጀመሩን ይናገራሉ። በዚህም የአካባቢው ማኅበረሰብ ልክ እንደ ወፍጮ ቤት እንሰቱን በጋሪ ይዞ ወደ በማዕከሉ በመሄድ አስፍቆ ወደ ቤቱ የሚመለስበት ሁኔታ መመቻቸቱንም ይጠቁማሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ አንድ አርሶ አደር ማሽኑን ለመግዛት የአቅም ውስንነት ሊኖርበት ይችላል፤ በመሆኑም ቴክኖሎጂው በማዕከል በኩል ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ማድረጉ ሁሉንም ተጠቃሚ ማድረግ ያስችላል፤ ተመራጭም ነው። በዚህም ጥሩ ለውጦች እየታዩ ናቸው። ማዕከሉ እስከ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ ያስችላል። አርሶ አደሮች ማሽኑን ገዝተው ለመጠቀም ከፈለጉም በኅብረት በመሆን ብዙም ኪስ በማይጎዳ ዋጋ ገዝተው መጠቀም ይችላሉ።

ዶ/ር አዲሱ እስካሁን ዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ለመስጠት ከአጋር አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ መሆኑን ይገልጻሉ። ማዕከላት የመገንባቱ ሂደት ከኢትዮጵያ ባዮ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ከሌሎችም አጋር አካላት ጋር በመተባበር እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

የማዕከላቱ ግንባታ በዶርዜ አካባቢ ሙሉ ለሙሉ አገልግሎት ላይ ውሏል የሚሉት ዶ/ር አዲሱ፣ ‹‹ክርስቲያን ኤድ›› ከተሰኘ ግብረሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር በወላይታ ሁለት ማዕከላት መገንባታቸውንም ይጠቁማሉ። በማዕከላቱም ለ1ሺ280 አርሶ አደሮችና ወጣቶች የሥራ እድል መፈጠሩን ይጠቁማሉ።

በቅርቡ ደግሞ ሦስት ማዕከላት በጋሞ ለመገንባት በሰፊው እየተሠራ መሆኑን ይናገራሉ። ማዕከላቱ ሲገነቡ ይሰጣሉ ተብሎ ከተገመተው በላይ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ሊሰጡ እንደሚችሉም ዶ/ር አዲሱ የሚናገሩት።

‹‹ ከእንሰት ቆጮንና የመሳሰሉትን ለማምረት የኬሚካል ፣የማዳበሪያ እና የመሳሰሉ ምንም አይነት ዶላር ውጭ አናወጣም ›› ሲሉ ዶ/ር አዲሱ ይናገራሉ፤ እንሰት ሙሉ ለሙሉ ሀገር በቀል እጽዋት መሆኑንም ጠቅሰው፣ ‹‹እንደ ሀገር በምግብ ራሳችንን ለመቻል በሚደረገው ጥረት ላይ አጋዥ በመሆን ትልቅ አስተዋፅዖ ያበረክታል›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

የቴክኖሎጂ ማስፋፊያዎች ለመሥራት ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ከአጋር አካላት ጋር እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች መኖራቸውም ጠቅሰው፣ እስካሁን ሥራ የጀመሩና ወደ ሥራ እየገቡም ያሉ ማዕከላት መኖራቸውም አስታውቀዋል። በቀጣይ ደግሞ ተጨማሪ ማዕከላትን በመገንባት በአጭር ጊዜ ወደ ሥራ እንደሚገቡ እንደሚደረግ አመላክተዋል።

ዶ/ር አዲሱ እንደሚሉት፤ አርሶ አደሩ በቴክኖሎጂው ለመጠቀም ከፍተኛ ፍላጎት አለው። በተለይ ቴክኖሎጂዎቹ ተሞክረው ያመጡትን ውጤት ሲያዩ በፍጥነት ተግባራዊ እንዲደረግላቸው ይፈልጋሉ። የማዕከሉ ተጠቃሚዎችም በዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በመሆናቸው ለውጥ ማምጣታቸውን ይናገራሉ። በተለይ ደግሞ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን እንደቆጠበላቸው እንዲሁም ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንደሆነላቸው ይገልጻሉ ።

ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚያገኙት ቆጮ ጥራቱን የጠበቀ ከመሆኑም በላይ ገበያ ላይ የተሻለ ዋጋ ያገኙበታል የሚሉት ዶ/ር አዲሱ፤ ቴክኖሎጂ ሕይወታቸውን በመቀየር ረገድ ለውጥ መምጣት መቻሉን አይተናል ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ቴክኖሎጂው ያልደረሰባቸው አካባቢዎች በመኖራቸው ቴክኖሎጂውን በማስፋፋት በኩል ትልቅ ሥራ ይጠይቃል። የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ ለወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እነዚህን ማዕከላት በየቦታው በማስፋፋት ጥቅም ላይ በማዋል አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት ይቻላል።

ቴክኖሎጂው ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት ለሙከራ ብዙ አይነት ማሽኖች መሥራታቸውን የሚገልጹት ተመራማሪው፣ እነዚህ ማሽኖች ሙያዊ እውቀትን የሚጠይቁ በመሆናቸው እናቶች እንዲጠቀሙበት የሚያስችሉ አልነበሩም ይላሉ። አሁን ጥቅም ላይ ውለው አገልግሎት እየሰጡ ያሉት ማሽኖች ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ በትንሽ ስልጠና እናቶች ራሳቸው እንደፈለጉ ሊሠሩባቸው የሚችሉ መሆናቸውን ያብራራሉ ።

በዶርዜ ማዕከል የተገኘው ተሞክሮ እንደሚያሳየው በባሕላዊ መንገድ እንሰት ይፍቁ የነበሩ እናቶች፤ ስልጠና ከወሰዱ በኋላ በአጭር ጊዜ የማንንም እገዛ ሳይፈልጉ በማሽኖቹ በቀላሉ ራሳቸው እየሠሩ መሆናቸው አመላክተዋል። ይህም ለመጠቀም ምቹና ቀላል ማሽኖች ተደራሽ ስለመሆናቸው ማሳያ ነው ብለዋል ።

ዶ/ር አዲሱ እንደሚሉት፤ ዩኒቨርሲቲው እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በመሥራቱ ሀገር አቀፍ ፣ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ እውቅናም አግኝቷል። የማኅበረሰቡን ሕይወት ከመለወጥ ፣የምግብ ዋስትናን ከማሻሻል አንጻር ብዙ እውቅናዎች እንዲኖሩት አድርጓል። የቴክኖሎጂ ውጤቶቹንም በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት በማስመዘገቡ አምስት የሚደርሱ ቴክኖሎጂዎች የአዕምራዊ ንብረት ጥበቃ እንዲደረግላቸው መደረጉን አስታውቀዋል። ቴክኖሎጂዎቹ በሰፊው ተመርተው ሁሉም እንሰት አልሚ ኅብረተሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ሰፊ ሥራዎችን እንደሚጠይቅ ዶ/ር አዲሱ አስገንዝበዋል።

እንደ ተመራማሪው ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እንሰት በአራት ክልሎች (በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እና ኦሮሚያ ) ይለማል፤ በእነዚህ ክልሎቹ ሁሉ ቴክኖሎጂዎቹ ተባዝተው በስፋት ተደራሽ እንዲሆኑ ቢደረግ በተለይ ለወጣቶች የሥራ እድል የሚፈጥሩ ናቸው። ከዚህም ባሻገር እንደሀገር በምግብ ራስን ለመቻል የሚደረገውን ጥረትም አንድም የውጭ ምንዛሪ ሳይወጣበት ማሳካት ይቻላል።

አሁን ላይ ዩኒቨርሲቲው ካለው የሀብት ውስንነት አንጻር ቴክኖሎጂውን ለሁሉም ተደራሽ ማድረግ አይችልም ያሉት ዶክተር አዲሱ፤ በተለይ አጋር አካላት ከዩኒቨርሲቲው ጋር ተባብረው ቢሠሩ ቴክኖሎጂዎቹን ለበርካታ እንሰት አልሚ አርሶ አደሮች ተደራሽ በማድረግ በርካታ ወጣቶችንም ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## የሽግግር ፍትህ - በባለሙያዎች አተያይ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

‹‹በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ ማዕቀፍ አማራጮችን›› የያዘውን ሰነድ የፍትሕ ሚኒስቴር ታህሳስ ወር መጨረሻ ላይ ይፋ አድርጓል። በ54 ከተሞች ብሔራዊ ምክክር እንደሚደረግም ተገልጿል። በዚህም መሰረት የማስጀመሪያ መርሐ ግብር ተካሂዷል።

የሽግግር ፍትህ ዓላማው የተሟላ ሰላምን ማስፈን ነው። ከእርስ በእርስ ጦርነት፣ ግጭት እና ጭቆና በመውጣት ፣ በፖለቲካና በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ትርጉም ያለው ሽግግር ማድረግ ስለመሆኑ ሰነዱ ያመለክታል። ይህን ሥርዓት ለማስፈን በሞከሩ ሀገራት የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ተግባራዊ በማድረጋቸው የሽግግር ፍትህ ሥርዓት መዘርጋቱ ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ እና ፍትህ በማስገኘት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳበረከተም የሽግግር ፍትህ ሰነዱ ያመለክታል። በሌላ በኩል ደግሞ በሽግግር ውስጥ ያለ ማህበረሰብ ከነበረበት ሁኔታ ሲወጣ ወይም ለመውጣት በሚደረግ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥመው ፈተና በግጭት፣ በጦርነት ወይም ጨቋኝ ሥርዓት በነበረበት ወቅት ለተፈፀመ ጥቃት፣ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትና በደል የተሟላ መፍትሄ መስጠት አለመቻል አንዱ ችግር እንደሆነም ሰነዱ ያብራራል።

ለመሆኑ የሽግግር ፍትህን ለማስፈን ከማን ምን ይጠበቃል፤ ምን ያክል ጊዜ ሊወስድ ይችላል፤ ምን ዓይነት ጉዳዮችን ሊመለከት ይችላል በሚሉት ላይ ባለሙያዎች ምሁራዊ ሃሳባቸውን ይሰጣሉ።

የሕግ ባለሙያውና የፌዴራሊዝም መምህሩ አቶ ኑሩ መኩሪያ የሽግግር ፍትህ በታሪክ አጋጣሚ ወይንም ደግሞ ባልታሰቡ ሁኔታዎች ውስጥ የተፈጠሩ ግጭቶችን፣ አለመግባባቶችን፣ የጸጥታ መደፍረስና ጉዳቶችን፤ የህሕይወት መጥፋት፤ የንብረት ውድመትና በአጠቃላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የሥርዓት ግድፈቶችና ለማረምና በዚያ ውስጥ ሰለባ የሆኑ አካላት ፍትህና ርትዕን እንዲያገኙ እንዲሁም የተረጋጋ ሰላም እንዲመጣ የሚደረግ ጥረት መሆኑን ያብራራሉ።

የሽግግር ፍትህ ፖለቲካዊ፣ ማህረሰባዊና ምጣኔ ሀብታዊ አንድምታ በውስጡ ታሳቢ እንደሚያደርግም ይጠቁማሉ። በዚህ ሂደት ሆን ተብሎ የመብት ጥሰት የደረሰባቸው አካላት እንዲካሱ ወይንም ጉዳት ያደረሰባቸው አካላት ይቅርታን በመጠየቅ ወደ ቀደመ ማህበረሰባዊ እሴት እና አንድነት እንዲመለሱ በማድረግ የሚኖረው ማህበረሰባዊ እሳቤ የላቀ ስለመሆኑ ይናገራሉ። በመሆኑም የሽግግር ፍትህ ከማህበረሰባዊ እሳቤ አኳያ ትርጉሙ የተለቀና ሂደቱ ይህን ለማንበር የሚደረግ ሠላማዊ ሂደት እንደሆነ ይናገራሉ።

በሽግግር ፍትህ ውስጥ ምጣኔ ሀብታዊ አንድምታ ያላቸው ተግባራትም ሊከወኑ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ- አቶ ኑሩ። ለአብነትም ሆን ተብሎ ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት የተገለሉ አካላት በሽግግር ፍትህ የመደመጥ ዕድል ያገኛሉ። ተጎድተናል ብለው የሚያስቡትን ሁኔታ የሚያሳዩበትና በቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገትና ሽግግር ተጠቃሚ የሚሆኑበት ዕድል የሚመቻችበት ነው። ይህም በኢኮኖሚ እሳቤ ተጎድተናል ብለው የሚያስቡ አካላት በአገር ሁለንተናዊ ተሳትፎ ውስጥ ተዋናይ የሚያደርጋቸው ይሆናል።

ኢትዮጵያን በመሰሉ ፌዴራላዊ ሥርዓትን በሚከተሉ አገራት ደግሞ ሽግግር ፍትህ በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን ያምናሉ። ለአብነትም በታሪክ አጋጣሚም ይሁን በሌሎች እሳቤዎች አንዱ ማህበረሰብ ከሌላው የተገለለበት፤ የተጎዳበት አሊያም በእኩል ዓይን አልተዳኘሁም ብሎ የሚያምንበት ዕድል ካለ ሥርዓቱን ለማስቀጠል ፈተና ይሆናል። በመሆኑም የሽግግር ፍትህ የፌዴራል ሥርዓቱንም ለማስቀጠል፤ ለማጠናከርና አብሮአዊነትን የበለጠ ለማስተሳሰር ፋይዳው የጎላ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥም በርካታ አገራትም ያለፉ መሆኑም በመጠቆም አሁናዊ የምጣኔ ሀብት ዕድገታቸው፤ ማህበረሰባዊ እሳቤያቸውና መተማመናቸው በጣም የላቀ እንደሆነም ያብራራሉ።

> በሽግግር ፍትህ ውስጥ ችግር ወይንም ግጭት በፈጠሩ ሁለት እና ከዚያ በላይ አካላት መካከል ፍትህ ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ውስጥ በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ወደ አለመግባባት ያስገባቸው መሰረታዊ ነገር ወይንም የሁኔታዎች ቅድመ ሁኔታ ምንድን ነው የሚለው ነው

በአጠቃላይ ብዙሃኑ አምነውበት የሚሰፍን ሽግግር ፍትህ ተበዳዮችን በይቅርታ ካሳ አሊያም ተመጣጣኝ በሆነ ሁኔታ ቁሳዊና ሞራላዊ ካሳ የሚያገኙበት ከመሆኑም በተጨማሪ አገር ከማስቀጠልና አገራዊ የፖለቲካ ሥሪትን ከማጠናከር አኳያም የላቀ ትርጉም እንዳለው ያስረዳሉ ።

የሕግ ባለሙያ እና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ማዕከል ዋና ዳይሬክተር አቶ ያሬድ ኃይለማርያም በበኩላቸው፤ የሽግግር ወቅት ፍትህ ሂደት ነው ይላሉ። በአንድ አገር በግጭትም ሆነ በሌላ አጋጣሚ አስከፊ የሆነ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ይፈጸም ከነበረ ለአጭርም ሆነ ለረዥም ጊዜ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ወደሚገነባበት ሠላማዊ ሁኔታ ለመሸጋገር የሚደረግ ሂደት ስለመሆኑ ይጠቁማሉ።

የሰብዓዊ መብት ጥሰት የተፈጸመባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ይኖራሉ። የሕግ እና የመብት ጥሰት የፈጸሙም ስለሚኖሩ ‹የተበደሉ ሰዎች ከዚህ አስቸጋሪ ወቅት የሚያልፉበት መንገድ ነው።› ባይ ናቸው። ለሽግግር ወቅት ፍትህ መሠረት የሆኑ ጉዳዮችም መጀመሪያ ላይ የሚቀመጠው ፍትህ እና ተጠያቂነትን ማስፈን ነው። እርቅ ማውረድ ቀጥሎ የሚመጣ ነው። የተፈጸሙ ጥሰቶች በአግባቡ ተሰንደው በመልክ በመልክ እንዲታወቁም ይደረጋል። የተበደሉ አካላት በዋናነት አንድም ለጉዳታቸው ተመጣጣኝ ካሳ የሚያገኙበት፣ ሁለትም በአጥፊዎች ይቅርታ እንዲጠየቁ የሚደረግበት ሂደት ስለመሆኑም አቶ ያሬድ ለቢቢሲ አማርኛው በሰጡት ማብራሪያቸው ያስረዳሉ።

የሽግግር ፍትህ በውስጡ ትልቅ የሕግ እሳቤዎችን ያየዘ ስለመሆኑ የሚናገሩት ደግሞ የሕግ ባለሙያው አቶ በፍርዴ ጥላሁን ናቸው። የሽግግር ፍትህ በምን ያክል ጊዜ ይጠናቀቃል ብሎ ለመወሰን ግን ሂደቶች ይወስኑታል ይላሉ። የሽግግር ፍትህን ለማስፈን በመጀመሪያ ተፈጸሙ የተባሉ የሕግ ጥሰቶች ምንድን ናቸው ብሎ ማየት፣ መገምገም፣ መረዳትና መተንተን ይፈልጋል። በዚህ ሂደት በደፈናው ፍትህ ይሰፍናል ተብሎ የሚቀመጥበት ሳይሆን ላለፉት ጥፋቶችና ግድፈቶች የትኛው አካል ምን ድርሻ ነበረው የሚለውን ማየት ተገቢ ነው።

በአገሪቱ ሕገ መንግሥት እና ዓለም አቀፍ ሕግ ጥሰቶችን የሚዳኙበት፣ የሚመዘኑበትና ፍትህ የሚሰፍንበት የሕግ መስመሮች በጥልቀት ከተመረመሩ በኋላ እነዚህ ጥፋቶች እንዳይደገሙ ከየትኛው አካል ምን ይጠበቃል የሚለውም በሂደቱ ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ስለመሆናቸው ያብራራሉ። ለአብነት በሽግግር ፍትህ ውስጥ ችግር ወይንም ግጭት በፈጠሩ ሁለት እና ከዚያ በላይ አካላት መካከል ፍትህ ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ውስጥ በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ወደ አለመግባባት ያስገባቸው መሰረታዊ ነገር ወይንም የሁኔታዎች ቅድመ ሁኔታ ምንድን ነው የሚለው ነው ። በዚህም ውስጥ ታሪካዊ ቁርሾዎች፣ የፖለቲካዊ መሪዎች ሚና፣ የአገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓት ሥሪትና የሕግ የበላይነት የሚከበርበት ደረጃ፣ የማህበረሰቡ እሴትና ተግባቦት ያለበትን ደረጃ እንደመነሻ ማወቅና ለሽግግር ፍትህ እንደ አንድ እርሾ መጠቀም ይገባል።

እንደ አቶ በፍርዴ ገለጻ ከሆነ፤ የሽግግር ፍትህ በራሱ ከአንዱ ሁኔታ ወደ ሌላው ምዕራፍ የሚደረግ ሽግግር ወይንም ደግሞ የፖለቲካዊ አተያይና ማህበረሰባዊ አኗኗር የሚያመራ በመሆኑ የራሱ ሂደት ያለው መሆኑን ያብራራሉ። የፈጠነ ሽግግር ፍትህ ለማስፈን ያለፉት ሂደቶች ምን ነበሩ የሚለውን በሚገባ መገምገም ተገቢ ነው። በዚህም ውስጥ የተፈፀሙ ግድፈቶችና ስህተቶች ብዙም አጨቃጫቂ ካልሆኑ የፈጠነ የሽግግር ፍትህን ለማስፈን ያግዛል። ይሁንና ነገሮች በተቃራኒው ሆነው ከሆነ ዓመታትን የመውሰድ ዕድል ሊኖራቸው ይችላል። ለአብነትም ከፍተኛ የሆነ የጦር ወንጀል፤ ዘር ማጥፋትና የመሳሳሉት ሂደቶች ካሉ እነዚህን ማስታመም፤ በሂደት ውስጥ በልዩ ሁኔታ የሚካሱበትን መለየትና አግባብ የሆነ ፍትህ አሊያም ሽግግር ሂደትን ለማስፈን ሲባል ጽሞና ያስፈልጋል። ከዚህም በተጨማሪ ማህበረሰቡና በአጠቃላይ ሂደቱ ላይ የሚሳተፉ አካላት ስለ ሽግግር ፍትህ ያላቸው ግንዛቤ እና ፍላጎትም ሁኔታዎችን የማቅለል ወይንም ደግሞ ችግሩን የባሰ የማወሳሰብ አቅም አለው የሚል ዕምነት አላቸው ይላሉ አቶ በፍርዴ።

እንደ ምሁራኑ ሃሳብ ከሆነ፤ የሽግግር ፍትህ በአንድ አገር ውስጥ በማህበረሰባዊ፤ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ክዋኔዎች ውስጥ በታሪክ አጋጣሚ የተፈጠሩ ቀውሶችን አሊያም ደግሞ ግጭቶችን ለመፍታት ሲባል የሚደረግ ሠላማዊ የፍትህ ሥርዓት ነው። ይህን ለማስፈንም ሂደቶችን የሚጠይቅ ሲሆን እንደተፈጠረው ቀውስ ወይንም አለመግባባት የሽግግር ፍትህ ሥርዓቱም የመፍጠን እና የመዘግየት ዕድል አለው። የሆነው ሆኖ ግን መሰል ጉዳዮች አለመረጋጋት ውስጥ የገቡ አገራትን ወደ ተረጋጋና ሠላማዊ ሁኔታ የመመለስ አቅማቸው እጅግ የላቀ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

ኢትዮጵያ ያዘጋጀችው ‹‹የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች›› የሚለው ሰነድም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በተለያዩ የዓለም ሀገራት የተለያየ ይዘት ያላቸው የሽግግር ፍትህ ስራዎች ተግባራዊ ሆነዋል። በተለይም በደቡብ አሜሪካና በአፍሪካ ሀገራት የሽግግር ፍትህ አሰራሮች በተለያየ መጠን ተተግብረው በርካታ ተሞክሮዎች ተቀምረዋል። ከነዚህ አገሮች የተሳካ የሽግግር ፍትህ ልምድም ሌሎች ሀገራት ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራት እና ሊከተሏቸው የሚገቡ ሂደቶችን ለመለየት ተችሏል ሲል በሽግግር ፍትህ ሰላምን ለማስፈን እየተሄደበት ያለውን ቁርጠኝነት ያስገነዝባል።

በሽግግር ውስጥ ያለ ማህበረሰብ ከነበረበት ሁኔታ ሲወጣ ወይም ለመውጣት በሚደረግ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥመው ፈተና በግጭት፣ በጦርነት ወይም ጨቋኝ ሥርዓት በነበረበት ወቅት ለተፈፀመ ጥቃት፣ መጠነ-ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እና በደል የተሟላ መፍትሄ መስጠት መቻል ነው። ይህም በዋናነት ሙሉ ፍትህ የሚሰጥበትን መንገድ መዘርጋት እና ማህበረሰቡ ተመልሶ ወደቀደመ ሰላሙ እንዲመለስ ለማድረግ የሚያስችል ዘላቂ ሰላም፣ እርቅ፣ መረጋጋት እና የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት መገንባት የሚቻልበትን ሁኔታ የሚመለከት ስለመሆኑ በማስገንዘብ፤ ኢትዮጵያም ይህን ለመተግበር መወሰኗን ይጠቁማል።

ማህበራዊ

# ሴቶች


ጋዜጠኛ አባይነሽ ብሩ


ጋዜጠኛ ዘለዓለም ጌታቸው


ጋዜጠኛ የምወድሽ በቀለ


ጋዜጠኛ ዙበይዳ አወል

## ሴቶች በማስታወቂያዎች የሚሳሉባቸው መንገዶች

ሰላማዊት ውቤ

«ብዙዎቻችን ልብስ ማጠብ፤ ልጅ መንከባከብና ምግብ ማዘጋጀት ለሴቶች ብቻ ተለይተው የተሰጡ የቤት ውስጥ የሥራ ዘርፎች ይመስሉናል።በቴሌቪዥን መስኮት የምናያቸው ማስታወቂያዎችም እንዲህ ዓይነቶቹን ፍረጃዎችን በማበረታታት የሚያስቀጥሉ ነው የሚመስሉት። ለምሳሌ ኦሞና ዳይፐር እንዲሁም ልጅ ማስከተብና ማሳከምን የሚመለከቱ ማስታወቂያዎች አብዝተው በሴት ነው የሚተዋወቁት። መኪና መንዳትና ቅንጡ አፓርታማ ማስተዋወቅን ደግሞ ለወንዶች ብቻ የተተወ ይመስላል። ይሄ ልክ ነው ብዬ አላምንም። አሁን ላይ እንደ አገር የጾታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ከላይ ከፖለቲካ አመራሩ ጀምሮ ታች እስከ ወረዳ ድረስ እየተሰራ ያለበትን ተግባር ያደናቅፋል። እኩል ተሳትፏችንንም ቀድሞ ማህበረሰቡ ይሄ የሴት፤ያ የወንድ ብሎ በመፈረጅ ወደ ኋለኛው አስተሳሰብ በመመለስ እድገታችንን ይጎትታል።

ይሄም ብቻ ሳይሆን ሴቶች ካለባቸው የኢኮኖሚ ችግር የተነሳ በማስታወቂያ ሲሳተፉ ራሳቸውን እንደሸቀጥ እንዲያቀርቡ የሚገደዱበት ሁኔታ ይስተዋላል።ይሄን እንደጥቃት ነው የማየው።በማስታወቂያ ብቻ ሳይሆን በቃለ ምልልስ ወቅት አንዳንድ ጋዜጠኞች ለሴቶች የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ሴቶችን ዝቅ የሚያደርጉ፤ የሴቶች እኩልነትና መብትን ያላገናዘቡም ይመስሉኛል። ለምሳሌ ትልቅ ስልጣን ላይ ያለችና ስኬታማ የሆነችን ሴት ለምን አላገባሽም? ብሎ መጠየቅ ልክ አይደለም» ትላለች ለረዥም ጊዜ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ስታገለግል የቆየችውና በአሁኑ ሰዓት የኮሚኒኬሽን አማካሪ ሆና በግሏ እየሰራች የምትገኘው አንጋፋዋ ጋዜጠኛ አባይነሽ ብሩ።

አባይነሽ እንደምትመክረው አመራር ላይ ላሉ እና ብዙ ሥራ ለሠሩ እንዲሁም ውጤታማ ለሆኑ ሴቶች ቃለ ምልልስ ሲደረግ በሴትነታቸው ያለፏቸውን ተግዳሮቶች እንዴት አድርገው እንደ ተቋቋሙት ቢዳስሱ ይመረጣል። ጥያቄዎቹ የሚነሱበት አግባብ ወደ ታች ዝቅ በማድረግ ሳይሆን ጥንካሬአቸውን አጉልቶ በማውጣት መሆን አለበት። ማስታወቂያም ዋና ዓላማው ከሽያጭና ገንዘብ ከማግኘት ጋር ቢያያዝም የሴቷን ስብዕና እና ማንነት ያከበረና የስርዓተ ጾታን እኩልነት ያገናዘበ መሆንይኖርበታል። ሥራውም የማስታወቂያ ሕግና ስርዓትን ተከትሎ መሠራት አለበት።

ይሄ የሴት ወገንተኝነትን በማረጋገጥ በሕብረተሰብ ውስጥ የጾታ እኩልነትን ለማምጣት ብቻ ሳይሆን፤ ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊና ሁለንተናዊ ዕድገት በእጅጉ ያስፈልጋል። ሆኖም በእኛ አገር በየትኛውም መንገድ በተለይ መንግስት በሚቆጣጠራቸው ሚዲያዎች ሲተላለፉ የሚስተዋሉ ማስታወቂያዎች ማሟላት የሚገባቸውን አሟልተው የሚሠሩና የሚተላለፉ አይመስሉም። «ማስታወቂያ የሽያጭ የግዢና የገንዘብ ጉዳይ ስለሆነ አንድ ምርት ለመሸጥ ሲባል በሚሠራ ማስታወቂያ ውስጥ ሴቶች ይሳተፋሉ። የሚሳተፉት ሴቶች ግን በምን መንገድ ነው የሚሳተፉት? ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን» የምትለው አንጋፋዋ ጋዜጠኛ አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ልጅ ያላት እናት ከሴቷ ልጇ በተለየ ሁኔታ ወንድ ልጇ እንዲጠነክር የሚያስችል ገንቢ ምግብ ስትሰራለት የሚያሳይ ማስታወቂያ ለመታዘብ መቻሏንም ለአብነት ትጠቅሳለች።

በማስታወቂያው ለተመልካች የሚተላለፈው መልዕክት የሚያጠነክር ገንቢ ምግብ ለወንድ እንጂ ለሴት እንደማያስፈልግ ዓይነት መሆኑን ታወሳለች። አባይነሽ የስርዓተ ጾታ እኩልነት ላይ እንዲህ ዓይነት ክፍተት የሚፈጥሩ ማስታወቂያዎች በፍጹም መተላለፍ እንደሌለባቸው ታነሳለች።

በርካታ አንጋፋ ሴት ጋዜጠኞች የጋዜጠኛዋን አስተያየት ይጋሩታል። አስተሳሰቡንና አካሄዱን በሀሳብ መዋጋት እንደሚገባም ይመክራሉ። በተደራጀ መልኩ መቀልበስ እንደሚገባም ያነሳሉ። አንጋፋዋን ጋዜጠኛ አባይነሽን ያገኘንበትና ጉዳዩ ሲነሳ የሰማንበት የኢትዮጵያ መገናኛ ባለሙያ ሴቶች ማህበር (ኢትመባሴማ)፤ አንድ ጋዜጠኛ ለአንዲት ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን ላይ ላሉ አመራር ቃለ ምልልስ በሚያደርግበት ወቅት ለምን አላገባሽም? የሚል ዓይነት ጥያቄ ማቅረቡን አስመልክቶ ጋዜጠኛው ለሚሰራበት ድርጅት ደብዳቤ መጻፉን ለአብነት ያነሳሉ።

ኢትመባሴማ ጠቅላላ ጉባኤውን ባካሄደበትና ሀሳቡ ተነስቶ በነበረበት መድረክ ላይ ያገኘናት ጋዜጠኛና በአሁኑ ወቅት በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን የጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ ባለሙያ ሆና በማገልገል ላይ የምትገኘው ዘለዓለም ጌታቸው ከላይ የተነሳውን ሃሳብ አስመልክታ የሚከተለውን ሃሳብ ሰንዝራለች። አንድ ጋዜጠኛ ለአንዲት በከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ላሉ ሴት ያቀረበው ለምን አላገባሽም? ሳታገቢ እንዴት አመራር ሆንሽ? የሚል እንድምታ ያለው የሚመስለው ቃለ መጠየቅ አሁንም በጋዜጠኞች ጭምር የተዛባ አመለካከት እንዳለ የሚያሳይ ነው። «ለምን አላገባሽም?» ዓይነቱ ጥያቄ «አመራር የሚሆነው ያገባ ነው።» የሚል ዓይነት መልዕክት የያዘ ነው ትላለች። ጋዜጠኛዋ እንዲህ ዓይነቶቹ የጋዜጠኞች ጥያቄ ለሴቶች ባይቀርቡ እንደምትመርጥና ሆኖም በጋዜጠኛውና በአንዳንድ የመገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች ሲጠየቁ መስማቷን ታነሳለች።

«ጋዜጠኛው ይህንን ጥያቄ ያነሳው ተጠያቂዋ ሴት ስለሆነች ነው። ወንድ ቢሆን አያነሳውም። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት አንዳንዴ ሆን ተብሎ የሚደረግ ነው የሚመስለው። ያን ጥያቄ ሳያስበው ነው የጠየቃቸውና ያደረገው ማለት አይቻልም» ትላለች።

ጥያቄው ሕብረተሰቡ ሴት ቤቷን መምራት የምትችል ከሆነ የበለጠ ደግሞ ሕዝብንም፤ አገርንም ልትመራ ትችላለች የሚለውን ዕሳቤ የሚያፈርስና ከአመራርነት ጋር የሚያያይዘው ምንም አይነት ሳይንሳዊ መንገድ አለመኖሩን ትናገራለች። ይልቁንም ከጋብቻ ጋር ከማያያዝ ይልቅ ጋዜጠኛው አጉልቶ ማውጣት የነበረበት ኃላፊዋ በሥራቸው ጎልተው የወጡበትን ምስጢር መሆን እንደነበረበት ታወሳለች።

«በተለይ ሴቶች መምራት የምንችለው ገና በህፃንነታችን ከቤታችን ጀምሮ ነው» ትላለች ጋዜጠኛ ዘለዓለም ጌታቸው። አመራርነት ሴቶች ወላጆቻቸው የሚሰሩትን ሥራ እየሰሩና እህትና ወንድሞቻቸውን እያሳደጉ፤ ትምህርት ቤት አለቃ እየሆኑና እያዳበሩ የሚያመጡት ሂደት እንደሆነም ትናገራለች። በመሆኑም የመሪነት ጉዳይ በዕውቀት ወይም በልምድ የሚመጣ እንጂ የግድ ስላገባችና ስላላገባች የሚመጣ እንዳልሆነም ታነሳለች። አክላም በዚሁ ጥያቄ መነሻነት እንደ ተቋም በቅርቡ ጎንደር ላይ እንዲሁም በተደጋጋሚ በሌሎች ቦታዎች እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎች መቅረብ የለባቸውም በሚል ብዙ ስልጠናዎች መውሰዳቸውንም አጫውታናለች።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት ክፍል የመጡ ባለሙያ ጋዜጠኛው ከከፍተኛ አመራሯ ጋር ያደረገውን ቃለ መጠይቅ ቪዲዮ መሰረት በማድረግ ስልጠናው መካሄዱንና እርምት የተወሰደበት መሆኑንም አውስታለች።ጋዜጠኞች ለሴቶች በተለይም ከፍተኛ ስልጣን ላይ ላሉና ትልቅ አገራዊ አበርክቶ ላላቸው ቃለ መጠየቅ ሲያደርጉ እንዴት መሆን አለበት የሚለውም ጥናት እየተካሄደበት መሆኑ መረጃው እንዳላት ነግራናለች።

አንጋፋዋ ጋዜጠኛና ደራሲ እንዲሁም አሁን ላይ «የሴቶች ይችላሉ» ማህበር መሥራችና ዳይሬክተር የምወድሽ በቀለ ስለ ሴቶች ሕብረተሰቡ ጋር ብቻ ሳይሆን ጋዜጠኞች ጋር ጭምር የተዛባ አመለካከት እንዳለ ትናገራለች። በሕብረተሰቡ ውስጥ ለሴቶች ያለው አመለካከት ብዙ ሥራና ዕውቀት የሚጠይቅ በመሆኑ አሁን ድረስ ሴቶችን የምናይበት አመለካከት በፍፁም መስተካከል አልቻለም። «ለዚህም ነው የተለያየን የሴት ማህበራት በየሙያችን ተጠናክረን እየሠራን የምንገኘው» ትላለች።

አንድ ጋዜጠኛ የሰራው ሥራ ወደ ሕብረተሰብ ከመሄዱ በፊት ኤዲተሮቹም ሊያዩት ግድ ነው። ሆኖም አሁን ላይ የሚወጡ ማስታወቂያዎች እና ጽሑፎች ሁኔታቸው ሲታይ ትክክል አይደሉም። ኤዲተሮች የሚያይዋቸውም አይመስሉም። እንደ ሴት ጋዜጠኞች ማህበር ይሄው ተገምግሟል። «ተግባራቱ የሴቶችን መብት እየሸረሸሩ ነው ብለን ስለምናስብ እንደ ሴት ጋዜጠኞች ማህበር ይሄ ችግር እንዲቀረፍ ሁላችንም በመነጋገር በጋራ እንሥራ የሚል እሳቤ ላይ ደርሰናልም» ብላናለች።

«እኔም እንደ አንጋፋ ባለሙያነቴ ይሄ ይሰማኛል። ምክንያቱም ሴቶች መከበር አለብን» የምትለው ጋዜጠኛ የምወድሽ ሴቶች ስለማግባትና አለማግባታችንና ስለ ግል ሕይወታችን ሳይሆን ሕብረተሰቡን በሙያችን በትክክልና በውጤታማነት እያገለገልን ስለመሆናችን ነው መዘገብ ያለበት ትላለች። አንዲት ሴት መሪ ናት ሲባል የመሪነትን ሚና አሟልታ ምን ሠራች የሚለው ሌሎች ሴት መሪዎች እንዲወጡ ማስተማሪያ በመሆኑ ግላዊና ከባለቤቷ ውጪ ሌሎች ሊሰሟቸው የማይገቡ ጥያቄዎች መቅረባቸው አግባብ አይደለም። ማህበሩ ተግባሩ እንዲታረም ጥያቄ ያቀረበውም ለዚህ ነው።

ጋዜጠኛ የምወድሽ አሁን ላይ ሴቶች በማስታወቂያዎች የሚሳሉበትንም አግባብ ከዚሁ ከተዛባ አመለካከት የፀዳ እንዳልሆነ ታነሳለች። በነዚሁ ማስታወቂያዎች ጉዳይም እንደ ሴት ጋዜጠኞች ማህበርና እንደራሷ ተቋም መወያየታቸውንና ብዙ መልፋታቸውንም ታወሳለች። ሴቶች ላይ የሚደርሱ ችግሮች በመበራከታቸውና ሴቶች በግልም በጋራም ተደራጅተው ሁሌ እነዚህ ችግሮች እንዲቀረፉ በተለያየ መንገድ ሲያነሱ በመስማታቸው አንዳንዶች የዚህ አገር ‹የሴቶች ችግር መቼ ነው የሚቀረፈው› እስከማለት ደርሰዋል። ‹እነዚህ ሴቶች አበዙት› ብለው የሚተቹም አይጠፉም።«ሆኖም ወድደን ሳይሆን መፍትሄ ስላላገኘን ነው። መፍትሄ እስካላገኘን ድረስ መነጋገር፤ ማስተማር፤ እኛም መማር አለብን» ትላለች።

እንደታዘበችው አሁን ላይ በተለይ ከማስታወቂያ ጋር ተያይዞ የሚሰራው ሥራ ኃይ ባይ ያለው አይመስልም። ሌላው ቀርቶ መንግስት ከሚቆጣጠራቸው መገናኛ ብዙኃን የሚወጡ ማስታወቂያዎች ብቻ ቢስተዋሉ በጣም ያሸማቅቃሉ። የሴቶችን መብት የሚያከብሩ አይደሉም። በመሆኑም የሚወጡ ማስታወቂያዎች ላይ በደንብ ትኩረት ቢሰጥ ጥሩ ነው። አለበለዚያ ልጆቻችን ይሄን እያዩ ነው የሚያድጉት። ነገ እነሱም ይሄን እንደ ጥሩ ነገር ስለሚወስዱት መዘዙ ለሴቶች ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ለማህበረሰቡና ለአገሪቱም ይተርፋል ትላለች።

«የቀድሞ የጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መዓዛ አሸናፊ ‹በበዓል ቀን ዶሮ ትሰሪያለሽ ተብሎ ለምንድነው የሚጠየቀው› ሲሉ እሰማ ነበር» ስትል አስተያየቷን የጀመረችው በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እያገለገለች የምትገኘው አንጋፋዋ ጋዜጠኛ ዙበይዳ አወል ናት። ዙበይዳ ጋዜጠኞች የተለያዩ ባለስልጣናትን በሚያነጋግሩበት ወቅት ሥራቸው ላይ ትኩረት አለማድረጋቸውንም ታነሳለች። እንዳከለችው በተለይ ውጤታማ ሴቶች ከሆኑ የሄዱበትና ለዚህ የደረሱበትን መንገድ ከማጉላት ይልቅ የግል ሕይወቷን የሚመለከት፤ አግብተሻል ወይ?፤ ፈተሻል አሉ፤ ስንት ልጅ አለሽ? ልጆችሽን እንዴት ነው የምታሳድጊው?፤ አልፈው ተርፈው ሙያ አለሽ ወይ?፤ ዶሮወጥ ትችያለሽ? የሚሉ ጥያቄዎች በብዛት እንደሚጠየቁ ትናገራለች። እነዚህ አንደኛ ግላዊ ጉዳዮች ናቸው። ሁለተኛ ወንዱ የማይጠየቀው ጥያቄ ነው። የቤተሰብና የቤት ጉዳይ በእኛ ማህበረሰብ በአብዛኛው ለሴቷ ስለተሰጠ ነው እንጂ የወንዱም ኃላፊነት ነው። አሁን ላይ አንዳንድ ባለ ስልጣናት በተለይም ሴት ባለስልጣናት ለቃለ ምልልስ ፈቃደኛ የማይሆኑት ለዚህ ነው። በመሆኑም በቃለመጠይቅ ወቅት ስኬቷን፣ ሥራዋን፣ ኃላፊነቷንና ውጤቷን አጉልቶ ማሳየት ይገባል ትላለች። በተለይ ጋዜጠኞች ላይ ያለው አመለካከት በጣም መቀየር እንዳለበት ትመክራለች። «ከማስታወቂያ ጋር ተያይዞ ብዙ ጊዜ ሴቶች ቅር የምንሰኝባቸው ችግሮች አሉ» የምትለው ዙበይዳ ማስታወቂያው ሳቢ እንዲሆን በማሰብ ሴቶች እርቃናቸውን ሆነው ሳይቀር በማስተዋወቅ የሚሳተፉባቸው ሁኔታዎች መስተዋላቸውን ታነሳለች። ለምሳሌ በጣም አጓጉል የሆነ ልብስ ለብሰውና ተኝተው ፍራሽ ማስተዋወቅ ከእኛ ማህበረሰብ፣ ከባህላችን፣ ከሐይማኖታዊ ስርዓታችን አንፃር አይሄዱም ትላለች። «ለሴት ልጅ ክብር ሊሰጣት ይገባ ነበር» የምትለው ጋዜጠኛዋ ቆንጆ መልክና ቅርጽ ያላትን ሴት የመምረጥና ውበቷን ቅርጿንና ሴትነቷን ማሻሻጫ አድርጎ ማቅረብ እየተለመደ መምጣቱን ታወሳለች።

ዙበይዳ እንደምትለው በጉዳዩ ከሚተላለፈው መልዕክት ወይም ደግሞ ከምርቱ ሳይሆን ከሴቷ ውበትና ቅርጽ ሽያጭ ጋር የተያያዘ እስኪመስል ድረስ ማስታወቂያዎቻችን በእንዲህ ዓይነቱ ይዘት የተቃኙ ናቸው። ቆንጆ ሴቶችን መርጦ ማስታወቂያዎችን ከማሠራት ባለፈ አንዳንድ እንደ ሳሙና ኦሞ ያሉና ከጽዳት ጋር የተያያዙ የምርት ሸቀጦችን በማስተዋወቅ ሂደት እንዲሁ ሴቷን ብቻ የመጠቀም፤ ልብስ ማጠብ የሴቷ ብቻ ኃላፊነት ማስመሰል፤ መኪናን ማስተዋወቅ ለወንዶቹ የመስጠት ሁኔታዎች እና ልጆቻችንም ሲያይዋቸው በቃ ይሄ ነው የሴቷ ሥራ ብለው እንዲስቡ የሚያደርጉ ማስታወቂያዎች ይስተዋላሉ። በመሆኑም እኛ አገር ያሉ ማስታወቂያዎች በደንብ መታየትና መፈተሽ አለባቸው። ምርትም ሆነ የትኛውም አገልግሎት ማስታወቂያ ለሕብረተሰቡ የሚሰጠውን ጥቅምና አገልግሎት ነው እንጂ ማስተዋወቅ የሚገባው ሌላ ተግባር አይደለምና ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ በመምከር ዙበይዳ አስተያየቷን ታሳርጋለች።

እኛም እንደታዘብነው ሴቶች በማጀት ብቻ ተከልለው እንዲኖሩ ተፅዕኖ የሚያደርጉ ድርጊቶች በርካታ ናቸው። ድርጊቶቹ በማጀት መከለላቸውን የሚያበረታቱ ብቻ ሳይሆኑ ሴቶችን አሁን ከደረሱበት የዕድገት ማማ ወደ ኋላ የሚጎትቱም ድርጊቶች በርካታ ናቸው። እነዚህ ድርጊቶች ደግሞ በሚዲያ ሲደገፉ ጉዳዩን ይበልጥ ያከብዱታል። ለዛሬ ሃሳባችንን እዚሁ ጋር ገታ እናድርግና በቀጣይ ጽሑፋችን በዚሁ ጉዳይ የሚመለከታቸውን ባለ ድርሻ አካላት አስተያየት ይዘን እንቀርባለን። ቸር ሰንብቱ።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የደርግ አብዮት በፈነዳበት ዘመን በ1966 ዓ.ም በተለይም እየተጋመሰ በሚገኘው መጋቢት ወር ላይ የወጡ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዘገባዎች የዛሬው ዓምዳችን መዳረሻ አድርገናቸዋል፡፡ ለትውስታ ከመራረጥናቸው ዘገባዎች መካከል ዓሣ ማስገር ላይ የነበሩ ተማሪዎች ባሕር ገብተው ሞቱ፤ ከተመን በላይ ዋጋ ያስከፈሉ ነጋዴዎች ተቀጡ፣ «ሌባን ሌባ ቢሰርቀው ምን ይደንቀው» እንዲሉ አበው ሌባዪቱን ሌባ ሰረቃት የሚል ዘገባም ይገኙበታል፡፡ የዘገባዎቹ ዝርዝር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

### ዓሣ በማስገር ላይ የነበሩ ተማሪዎች ባሕር ገብተው ሞቱ

ጎባ ፤(ኢ.ዜ.አ.) ዓሣ በማስገር ላይ የነበሩ ፫ ተማሪዎች ከሚያጠምዱበት ፫ ሜትር ጥልቀት ካለው ባሕር ገብተው መሞታቸው ተገለጠ፡፡

ዕድሜያቸው ከ፲፬ እስከ ፲፱ ዓመት የሆናቸው ክብረት አበበ ፤ አድማሱ ላቀውና ጥበቡ ታደሰ ይባሉ የነበሩት እነዚህ ተማሪዎች የሞት አደጋ የደረሰባቸው ባለፈው ቅዳሜ በባሌ ጠቅላይ ግዛት በፋሲል አውራጃ ጎባ ከተማ አቅራቢያ ከሚገኘው ሻያ ወንዝ አፋፍ ላይ ሆነው ዓሣ በማጥመድ ላይ እንደነበሩ ነው፡፡

በዚህም ዕለት ፫ቱ ተማሪዎች ከቤት ወጥተው ሳይመለሱ በመቅረታቸው ለ፫ ቀናት በተደረገው ፍለጋ አስከሬናቸው ፫ ሜትር ጥልቀት ካለው ሻያ ወንዝ ውስጥ ሊገኝ መቻሉን ታውቋል፡፡

ከዚያም አስከሬናቸው ጎባ ከተማ ወደ ሚገኘው ሆስፒታል ተወስዶ አስፈላጊው ምርመራ ከተደረገለት በኋላ እንዲቀበር ለየዘመዶቻቸው ተሰጥቷል፡፡

እንዲሁም አቶ ኃይሌ ደጨሞ ይባሉ የነበሩ የድንሾ ከተማ ነዋሪ ከአዲሱ ከተማ ወደ አሮጌው ከተማ ወደ ሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ሲሔዱ ከመኖሪያ ቤታቸው ለመድረስ በግምት ፩፻፶ ሜትር ያህል ሲቀራቸው ድልቃ በተባለው ወንዝ ውስጥ ገብተው ሞተዋል፡፡

በግምት የ፳፭ ዓመት ዕድሜ የነበራቸው አቶ ኃሌ ደጨሞ አስከሬናቸው አንድ ሜትር ጥልቀት ካለው ውሃ ውስጥ በሕዝብና በፖሊሶች ዕርዳታ ወጥቶ በክፍሉ ሐኪም በተደረገለት ምርመራ በሟቹ አስከሬን ላይ ምንም የአደጋ ምልክት ባለመታየቱ ምናልባት ለውሃ ዋና ገብተው ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ማሳደሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

**( መጋቢት 11 ቀን 1966 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### ከተወሰነ ዋጋ በላይ ያስከፈሉ ነጋዴዎች ቅጣት ተፈረደባቸው

አዲስ አበባ ፤ (ኢ.ዜ.አ.) አቶ ተካ አስፋው የልዕልት የሻሸ ወርቅ ይልማ ቡና ቤት ባለ ንብረት ፤ አቶ ደበበ ዓለማየሁ በአገር ግዛት ሚኒስቴር ግቢ ባላቸው ቡና ቤት ውስጥ አንዱን ጠርሙስ የሾላ ወተት ፳፭ ሳቲም መሸጥ ሲገባቸው በ፶ ሳንቲም ለሕዝብ ሲሸጡ በመገኘታው አንደኛ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሰው ቀርበው ተከሳሾቹ ጥፋታቸውን ስላመኑ እያንዳንዳቸው በ፳ ብር መቀጫ እንዲከፍሉ ተፈረደባቸው፡፡

እንዲሁም አቶ ፀጋዬ ሙሉነህ በመሥፍነ ሐረር መንገድ «ንጋት» እየተባለ የሚጠራው የልብስ ንፅህና መስጫ ባለንብረት ቀድሞ ለ ፩ ሙሉ ልብስ ፫ ብር ከ ፶ ያስከፍሉ የነበረውን ዋጋ በመጨመር ፬ ብር ሲያስከፍሉ በመገኘታቸው በዐቃቤ ሕግ ክስ ቀርቦባቸው ተከሳሹ ጥፋታቸውን ስላመኑ ፻ ብር መቀጫ እንዲከፍሉ የተፈረደባቸው መሆኑን የአንደኛ ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛ አቶ ግርማ ማን አግደው አስታውቀዋል፡፡

ይህ ቅጣት በተከሳሾቹ ላይ የተወሰነው የካቲት ፴ ቀን በዐቃቤ ሕግ ክስ ቀርቦባቸው በ፴፩ ኛው ዓመት ነጋሪት ጋዜጣ ዓዋጅ ቁጥር ፲፮ ፫፻፩ /፳፬ በአንቀጽ ፲፱ መሠረት ነው፡፡

ይህን የመሰለው ጥፋት በመሠረቱ ፲ ሺህ ብር ወይም በሁለት ዓመት እስራት ፤ በገንዘብ መቀጫ እና በእስራትም ከፍተኛ ቅጣት የሚያስቀጣቸው ሲሆን ፍርድ ቤቱ ግን የተከሳሾችን የኑሮ  የገቢ መጠን ፤ በዚህ ወንጀል አፈጻጸም ምክንያት ያገኙትን ጥቅም በመገመት መቅጫውን አቃሎ ከላይ የተጠቀሰውን ቅጣት የወሰነባቸው መሆኑን የአንደኛ ወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛ በተጨማሪ አረጋግጠዋል፡፡

**( መጋቢት 3 ቀን 1966 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### ሌባዩቱን ሌባ ሰረቃት

አሰላ ፤(ኢ.ዜ.አ.) በግርድና ተቀጥራ ከምትሠራበት ቤት ፪ ሺህ ብር ሰርቃ ስትኮበልል፤ የሰረቀችውን ገንዘብ በሌላ ሌባ የተሰረቀችው  ዘውዲቱ ሞላ ፤ በ፮ ወር እስራት እንድትቀጣ አሰላ ከተማ ያስቻለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ችሎት ፈረደ፡፡

ተከሳሽ ለእስራት ያበቃት ይህንኑ ገንዘብ የተሰረቀችው በአሰላ ከተማ በግርድና ተቀጥራ ትሠራበት ከነበረው አቶ ግርማ ድፋባቸው ቤት ፤ ባለፈው መጋቢት ፩ ቀን ፳፮ ዓ/ም / ሲሆን ፤እሷ ገንዘቡን ይዛ ወደ ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ግዛት ከኮበለለች በኋላ ፤ደብረ ብርሃን ከተማ ውስጥ ስትዘዋወር በጋሻው አጥላው በተባለው ልማደኛ ሌባ መሰረቋ ታውቋል፡፡

ከዚያም ዘውዲቱ ሞላ ሀብቷ በልማደኛ ሌባ መሰረቁን ለክፍሉ ፖሊስ አመልክታ ፤ በተደረገው መከታተል በጋሻው አጥላው ተይዞ ምርመራው ከተጣራ በኋላ ፤ ደብረ ብርሃን አስቻለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመቅረብ ጥፋቱ በማስረጃና በሕግ ምስክሮች በመረጋገጡ ፤ አንድ ዓመት እስራ እንዲቀጣ ሲፈረድበት፤ የተሰረቀውም  ገንዘብ ለባለቤቷ እንዲመለስ ታዘዘ። በዚህም መሠረት ዘውዲቱ ሞላ  በፍርዱ መሠረት ገንዘቡን ለመረከብ ስትሰናዳ ዋናው ባለ ገንዘብ አቶ ግርማ ድፋባቸው በክትትል ደርሰውባት ኖሮ ፤ አስቀድሞ ገንዘብ ከሳቸው የተሰረቀ መሆኑን ማስረጃ አቅርበው ዘውዲቱ ከነገንዘቡ እጅ ከፍንጅ ተያዘች፡፡ ከዚያም ተከሳሿ ወደ አሰላ ከተማ ተልካ ወንጀሉን በፈጸመችበት ክፍል ክስ እንዲቀርብባት ተደርጎ ፤ አድራጎቷ በማስረጃና በሕግ ምስክሮች በመረጋገጡ በ፮ ወር እስራት እንድትቀጣ የተፈረደባት መሆኑን አንድ የፍርድ ቤቱ ቃል አቀባይ አስታውቋል፡፡ በሁለቱ ሌቦች መቀባበል ከተሰረቀው ከዚሁም ፪ ሺህ ብር ውስጥ ፮፻፳፭ ብር ከ፳፭ ሳንቲም ሲባክን በመጨረሻ የተገኘው ተራፊ ገንዘብ ፩ ሺህ ፫፻፺፳ ብር ከ፸፭ ሳንቲምና በተሰረቀው ገንዘብ ተገዝተው በኤግዚቢትነት የቀረቡት ልብሶችና ዕቃዎች ለባለገንዘቡ ለአቶ ግርማ ድፋባቸው እንዲሰጡ ፍርድ ቤቱ በዚሁ ጊዜ አብሮ ማዘዙን ቃል አቀባዩ ጨምሮ ገልጧል፡፡

**( መጋቢት 27 ቀን 1966 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ

## በእስራኤል የመከላከያ ሚኒስትሩ መባረር ከፍተኛ ተቃውሞ ቀሰቀሰ

የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ የመከላከያ ሚኒስትሩን ማባረራቸውን ተከትሎ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለተቃውሞ አደባባይ ወጡ። የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት ዮአቭ ጋላንት ከሥልጣን የተነሱት በአገሪቷ ያለውን የፍትሕ ሥርዓት ለማሻሻል የወጣ አወዛጋቢ እቅድን ከተቃወሙ በኋላ ነው።

የሕግ ማሻሻያው መንግሥት ዳኞችን የሚሰይመውን ኮሚቴ ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠር የሚያስችሉ እቅዶችን የሚያካትት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሕጉ ፍርድ ቤቶች ለሥልጣን ብቁ አይደሉም የተባሉን መሪ ለማንሳት ሥራቸውን ፈታኝ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ማሻሻያው በሙስና ወንጀል ተከሰው በፍርድ ቤት ጉዳያቸው እየታየ ያለው የቤንያሚን ኔታንያሁ ፍላጎት እንደሆነ የሚያምኑትን አስቆጥቷል።

ኔታንያሁ ግን የሕግ ማሻሻያው ፍርድ ቤቶች ከአቅማቸው በላይ በሥራ እንዳይጨናነቁ ለማድረግ ያለመ እና በቅርብ በተካሄደው ምርጫ በሕዝብ ድምጽ የተሰጠበት ነው ብለዋል። ይሁን እንጂ ሰኞ ዕለት ጠዋት የእስራኤሉ ፕሬዚዳንት ኢሳቅ ሄርዞግ መንግሥት የሕግ ማሻሻያዎቹን እንዲያግድ ጥሪ አቅርበዋል።

ፕሬዚዳንቱ በትዊተር ገጻቸው ባሰፈሩት ጽሑፍ “ለእስራኤል ሕዝብ አንድነት እና ኃላፊነት ሲሉ የሕግ ማሻሻል ሒደቱን በአስቸኳይ እንዲያቆሙ እጠይቃለሁ” ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። ፕሬዚደንቱ በዚሁ ጽሑፋቸው “የእስራኤል ሕዝብ ዓይን እርስዎ ላይ ነው” ሲሉም አክለዋል።



አሜሪካ በበኩሏ በእስራኤል ያለው ሁኔታ እጅጉን እንዳሳሰባት ገልጻ፣ መስማማት ላይ እንዲደረስ ጠይቃለች። ተቃዋሚዎቹ የእስራኤልን ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለቡ፣ ብረቶችን እያጋጩ በእየሩሳሌም በሚገኘው የኔታንያሁ መኖሪያ ቤት አቅራቢያ ተቃውሟቸውን ያሰሙ ሲሆን፣ ከዚያም እስራኤል ምክር ቤት-ክኔሴት ለመድረስ የፖሊስ ኃይሎችን ጥሰው አልፈዋል።

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ለቢቢሲ ስትናገር “ኔታንያሁ እንደ ዴሞክራሲያዊ አገር ያለንን መስመር እያለፉ ነው” ብላለች። “ያለንን የመጨረሻውን ዴሞክ ራሲ እየተከላከልን ነው። በዚህ ሁኔታ መተኛት አልችልም። ይህንን እብደት እስከምናስቆም ድረስ ምንም መስራት አልች ልም” ስትልም ጨምራ ተናግራ ለች።

በቴል አቪቭ የሚገኝ አውራ ጎዳናም የአገሪቷን ሰንደቅ ዓላማ በሚያውለበልቡ ተቃዋሚዎች ከሁለት ሰዓታት በላይ ለሆነ ጊዜ ተዘግቶ ቆይቷል። የጸጥታ ኃይሎችም ተቃዋሚዎቹን ለመበተን ውሃ ተጠቅመዋል። የቀድሞ ወታደር የነበሩት የመከላከያ ሚኒስትር ጋላንት፣ አዲስ በወጣው የሕግ ማሻሻያ ደስተኛ አይደሉም።

ጋላንት ሕጉን በመቃወም ቅዳሜ ዕለት ባደረጉት ንግግር የእስራኤል የመከላከያ ኃይሎች በሕጉ የተቆጡ እና የተበሳጩ መሆናቸውን ተናግረዋል። ጋላንት በቴሌቪዥን ቀርበው ይህንን ሲናገሩ ከአገር ውጭ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ኔታንያሁ፣ ከዚህ በኋላ “እንደ መከላከያ ሚኒስትር በእርሳቸው ላይ እምነት አይኖረኝም” ብለዋል።

ሁለቱ ፖለቲከኞች የሊኩድ ፓርቲ አባላት ሲሆኑ የመከላከያ ሚኒስትሩ በአቋማቸው የተወሰኑ የፓርቲ አባላትን ድጋፍ ማግኘት ችለዋል። ሌሎች የቀኝ አክራሪዎች ደግሞ ሚኒስትሩ እንዲባረሩ ጠይቀዋል። መከላከያ ሚኒስትሩ፣ ከሥልጣናቸው ከተባረሩ በኋላ በትዊተር ገጻቸው “የእስራኤል ደኅንነት የሕይወቴ ተልዕኮ የነበረ እና ሁልጊዜም የሚሆን ነው” ሲሉ አረጋግጠዋል።

የእስራኤል ተቃዋሚ መሪ ያሪ ላፒድ በበኩላቸው የጋላንት መባረር ለመንግሥት “አዲስ ዝቅጠት ነው” ሲሉ ኮንነውታል። “ኔታንያሁ ጋላንትን ማባረር ይችላል፤ ነገር ግን እውነታውን መካድ አሊያም የጥምረቱን እብደት ለመቃወም የሚታገሉትን የእስራኤልን ሕዝብ ማባረር አይችሉም” ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አዲሱ ሕግ በዚህ ሳምንት መጨረሻ በምክር ቤት ድምጽ እንዲሰጥበት ይፈልጋሉ። የዋይት ሃውስ ቃል አቀባይ “በቅርቡ ፕሬዚዳንቱ ከጠቅላይ ሚኒስትር ኔታንያሁ ጋር እንደተነጋገሩት ዴሞክራሲያዊ እሴቶች የአሜሪካ እና የእስራኤል ግንኙነት መለያዎች ናቸው። አሁንም መቀጠል አለባቸው” ሲሉ በእስራኤል ባለው ሁኔታ አሜሪካ ስጋት እንደፈጠረባት ተናግረዋል።

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት “መሠረታዊ ለውጦች” በሰፊ ሕዝብ ድጋፍ ላይ መመሥረት አለባቸው ሲሉም ቃል አቀባይዋ አክለዋል። የእስራኤል መሪዎች በሚቻለው ፍጥነት መግባባት ላይ እንዲደርሱም ማሳሰባቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ትራምፕ«በመንግሥት ውስጥ ያለን ስውር መንግሥት ካላጠፋነው ያጠፋናል» አሉ

ትራምፕ በቴክሳስ ዋኮ ባደረጉት ቅስቀሳ፣ የባይደን አስተዳደር ዋይትሃውስ ዳግም እንዳልገባ የሀሰት ክስ እያቀነባበረብኝ ነው አሉ፡፡ ዶናልድ ትራምፕ በቴክሳስ ዋኮ ባደረጉት ቅስቀሳ፣ የተጀመረባቸው የወንጀል ምርመራ እና የክስ ሂደት “ፖለቲካዊ” ጫና መሆኑን ተናግረዋል።

ትራምፕ በሺዎች ለሚቆጠሩ ደጋፊዎቻቸው ካስተላለፉት የ 2 ስአት ገደማ መልዕክት አብዛኛውን ጊዜ የወሰደው በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርግ ክስ ሊመሰርቱባቸው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ የሕግ ባለሙያዎችን የወረፉበት ነው። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት “የባይደን አስተዳደር ዳግም ዋይትሃውስ እንዳልገባ የወንጀል ክሱን ሆን ብሎ አቀነባብሮብኛል”ም ነው ያሉት።

ህግን ለፖለቲካዊ ፍላጎት ማስፈጸሚያ እና የፖለቲካ ተቀናቃኝን ማሳደጃ አድርገዋል ያሉትን የባይደን አስተዳደር፥ ያለምንም ማስረጃ ክስ ለመመስረት እየተጣደፈ ነው ሲሉም ከሰዋል።




ትራምፕ ከ2016ቱ ምርጫ አስቀድሞ ከአንዲት ተዋናይት ጋር የነበራቸውን ግንኙነትን ለመደበቅ ገንዘብ ከፍለዋል በሚል በማንሃተን አቃቤ ህግ ምርመራ እየተደረገባቸው ሲሆን ሊታሰሩ እንደሚችሉ ተገልጿል።

የጆርጂያ አቃቤ ህግም ከ2020ው ምርጫ ጋር በተያያዘ የወንጀል ድርጊት ፈጽመዋል በሚል ፍርድ ቤት ሊያቆማቸው ነው ተብሏል። የቀድሞ ፕሬዚዳንት ባለፈው ሳምንት በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ “ልታሰር እችላለሁ” የሚል መልዕክት በመለጠፍም ደጋፊዎቻቸን ለአመጽ ዝግጁ እንዲሆኑ ማዘዛቸውን ነው ሬውተርስ ያስታወሰው።

የአሜሪካ ኢኮኖሚ መውደቅ እና የስራ አጥ ሰዎች ቁጥር መጨመርን በቅስቀሳቸው ያነሱት ትራምፕ፥ “በመንግሥት ውስጥ ያለ ስውር መንግሥትን ካላጠፋነው ያጠፋናል” ማለታቸውን አል ዐይን ዘግቧል።

# ስፖርት



## የሊግ ካምፓኒው በአጭር ጊዜ ስኬታማ ስራዎችን አከናውኗል

ብርሃን ፈይሳ

በምስራቅ አፍሪካ ተመራጭና አትራፊ ሊግ መመስረትን ዓላማው ያደረገው የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማህበር 4ኛ መደበኛ እና 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤውን ባለፈው ቅዳሜ አከናውኗል። ከተመሰረተ አጭር ጊዜ የሆነው ማህበሩ አዳዲስ የዳይሬክተሮች ቦርድንም አስመርጧል። ማህበሩ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ አዲስ ይሁን እንጂ ከጅምሩ አንስቶ እስካሁን ድረስ መልካም የሚባል ተግባራትን በመከወን ላይ ይገኛል።

ውድድሩ በዘመናዊ መልክ እንዲመራ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ዕይታን እንዲያገኝም የማህበሩ ሲሰራ ቆይቷል። ይህንን ሁኔታ ለማስቀጠል እንደሚሰራም በተመራጭ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላቱ በኩል አስታውቋል። ከካምፓኒው ምስረታ አንስቶ ያለፉትን ዓመታት በሰብሳቢነት ሲመሩ የቆዩት መቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ፤ በዚህ ምርጫ ላይም በኢትዮጵያ ቡና እጩ በመሆን ቀርበዋል። በምርጫውም 11 ድምጽ በማግኘት በድጋሚ ለአክሲዮን ማህበሩ የዳይሬክተሮች ምርጫ ውስጥ በመግባት በድጋሚ በሰብሳቢነት እንዲያገለግሉ ተመርጠዋል።

ለረጅም ዓመታት በስፖርት አመራርነት የቆዩት አንጋፋው ባለሙያ፤ ሊግ ካምፓኒው ከተቋቋመ ሶስት ዓመታትን ብቻ ያስቆጠረ ይሁን እንጂ በርካታ ነገሮች የተሰሩ መሆኑን ገልፀዋል። በቅድሚያ የተደረገው በአፍሪካ ትልቅ ከሚባል ተቋም ጋር አብሮ ለመስራት ከስምምነት መድረስ ስኬት ነው። ቀጣዩ ደግሞ ይህንን ተቋም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይ ማድረግ፣ ክፍያውን እንዲጨምር ማድረግ፣ ሜዳዎች ብቁ የሚሆኑ ከሆነ ደግሞ እንደሌሎች ሀገራት ማስታወቂያዎችን በዘመናዊ መንገድ ማስተላለፍ እንዲሁም ጨዋታዎችን ስፖንሰር የሚያደርጉ ባለሀብቶችን በመጋበዝ




**የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አክሲዮን ማህበር አዳዲስ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መርጧል፣**

ሊጉን ማሳደግ እንደሚሆን አስረድተዋል።

ይሁንና አሁንም ድረስ ያልተፈታውና በስፖርቱ የጎላ ተግዳሮት በመሆን የቀጠለው ከክለቦች ጋር የተያያዘ ሲሆን፤ በተለይ ራሳቸውን በገንዘብ አለመቻል ተጠቃሽ ነው። መንግሥት በዚህ ወቅት ከመሰረተ ልማት ተርፎ እግር ኳሱን በማስተዳደር አላግባብ የሆነ ወጪ የሚያወጣበት እንዳልሆነ ሰብሳቢው አብራርተዋል። በውጤት ከበርካታ ሀገራት ኋላ የሚገኘው የሀገሪቷ ስፖርት በክፍያ ግን ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፍ ነው። በመሆኑም ክለቦች ሊፈተሹና በተጨባጭ ራሳቸውን ወደሚችሉበት ሁኔታ መመለስ ያስፈልጋቸዋል።

የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ አክሲዮን ማህበር ስራ አስኪያጅ አቶ ክፍሌ ሰይፈ፤ ካምፓኒው አዳዲስ ነገሮችን ይዞ የመጣ መሆኑን ገልፀው፣ በስፖርት ንግድ ዘርፍ የተቋቋመ እንደመሆኑ በርካታ ስራዎች ተሰርተው በአሁኑ ወቅት መልካም በሚባል አቋም ላይ ሊገኝ መቻሉን አብራርተዋል። እንደ አቶ ሰይፈ ገለፃ፣ ሊግ ካምፓኒው በእግር ኳስ ስፖርት ለመሰል ተቋማት መሰረት ሊሆን የሚችል ስኬታማ ተቋም ነው። ምክንቱም በየዓመቱ 4 ሚሊዮን ዶላር በተጨማሪም በየዓመቱ 250ሺ ዶላር እየጨመረ አሁን ላይ 4 ነጥብ 5ሚሊዮን ዶላር ደርሷል፤ በቀጣዩ ዓመት ደግሞ 5 ሚሊዮን ዶላር ይደርሳል። ይህንን ሁኔታም በቀጣይ አሻሽሎ ስፖንሰር ለሚሆኑ ድርጅቶች መገኘት ይገባዋል። በመሆኑም በማዘውተሪያ፣ በተመልካቾች እና መሰል ነገሮች ላይ በመስራት ተጨማሪ ገቢ ማግኘት ይችላል። ለዚህ ደግሞ አዲስ የተመረጠው ቦርድ ከባድ ኃላፊነት ያለበት ሲሆን፤ ዘርፉ አዲስ እንደመሆኑ ከንግድ ሕጉ ጋር ተያይዞ የታዩ ክፍተቶችንም መድፈን አስፈላጊ ነው።

በሌሎች ሀገራት የእግር ኳስ ሊጎች ከሚያገኙት ገቢ መንግሥትን ከመደገፍ አልፈው በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችም አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። በአንጻሩ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ተደጋፊ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፤ በመሆኑም ይህ መቀየር ይኖርበታል። ይህንን ለመቀየርም አክሲዮን ማህበሩ ከሱፐር ስፖርት ጋር ባለው ስምምነት ጋር በተያያዘ እስካሁን ለማሟላት ያልተቻለው ጥራትን በሚመለከት ነው። ደጋፊ ላይም በተመሳሳይ ተጨማሪ ስራ አስፈላጊ በመሆኑ ስታዲየም ላይ መስራት የግድ ይሆናል።

በጉባኤው ላይ የታደሙት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጂራም ምርጫውን ተከትሎ ባስተላለፉት መልዕክት፣ ካምፓኒው ከተመሰረተ ጥቂት ዓመታትን ብቻ ቢያስቆጥርም ያካሄደው ጉባኤና ምርጫ ግን በግልጸኝነቱ ለሌሎችም አርዓያ ሊሆን የሚያስችለው መሆኑን ጠቁመዋል። አዲስ ለተመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትም በተለይ በክለብ ላይሰንሲንግ፣ በሴቶችና ታዳጊዎች ስፖርት እንዲሁም በእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩም ጠይቀዋል።


## የሀገር ውስጥ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 005/2015፤006/2015፤ እና 007/2015

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ በ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመት የሚከተሉትን የላብራቶሪ ግብዓቶችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በዚህም መሠረት በጨረታ መለያ ቁጥር 005/2015፤

ሎት 1- የኤሌክትሪካልና የኮምፒውተር ኢንጅነሪንግ ቤተ-ሙከራ ግብዓቶች አቅርቦት ግዥ

ሎት 2፡- የመካኒካል ቤተ-ሙከራ ግብዓቶች አቅርቦት ግዥ፣

በጨረታ መለያ ቁጥር 006/2015

ሎት 1- የስፖርት ሳይንስ ቁሳቁሶችና ትጥቅ ግብዓቶች አቅርቦት፣

ሎት 2፡- የጤና ሳይንስ ላብራቶሪ ዕቃዎችና ግብዓቶች አቅርቦት ግዥ

**በጨረታ መለያ ቁጥር 007/2015**

የኢንኩቤሽን ሴንተር ግብዓቶችና ማሽኖች አቅርቦት

(Incubation Centre equipment)

በሎት 1፡- የኢንኩቤሽን ሴንተር ግብዓቶችና ማሽኖች አቅርቦት

ዕቃዎችን በዘርፉ የተሰማሩ ሕጋዊ ድርጅቶችን በሀገር ውስጥ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሠረት፡-**

1. የዘመኑን ግብር የከፈሉ፣ የተጨማሪ እሴት ተመዝጋቢ የሆኑና የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ በዘርፉ በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ በመንግስት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን በe-GP ድረ ገጽ የተመዘገቡ፤ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እና ከግብር ነፃ ስለመሆናቸው ክሊራንስና ሌሎች አስፈላጊ ዶክመንቶችን ኮፒ አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር መረጃ የያዘውን የጨረታ ሰነድ ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ እስከ 16ኛው ቀን 4፡00 ሰዓት ድረስ አዲስ አበባ አዲሱ ገበያ አካባቢ ከፍ ብሎ በሚገኘው አደባባይ ወደ ግራ በመታጠፍ 200 ሜትር ገባ ብሎ እመቤት ሆቴል አጠገብ በሚገኘው የዩኒቨርስቲው ጉዳይ ማስፈጸሚያ ቢሮ የማይመለስ 200/ ሁለት መቶ ብር ብቻ/ በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ የበጀት ሂሳብ ቁጥር 1000021129171 በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ በማድረግ የጨረታ ሰነዱን መግዛት/መውሰድ/ ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጨረታ መለያ ቁጥር 005/2015 ለሎት 1፡- 100.000 (አንድ መቶ ሺህ ብር)፣ ለሎት 2፡- 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) የጨረታ መለያ ቁጥር 006/2015 ለሎት 1፡- 100,000 ( አንድ መቶ ሺህ ብር) ለሎት 2፡- 100,000 ( አንድ መቶ ሺህ ብር) ለሎት 2፡100,000 ( አንድ መቶ ሺህ ብር) ለጨረታ መለያ ቁጥር 007/2015 ለሎት 1፡- 100.000 (አንድ መቶ ሺህ ብር)፣ በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ ወይም ለ120 ቀን የሚቆይ የጨረታ ማስከበሪያ በዩኒቨርሲቲው ስም አሠርተው ማስያዝ አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዳቸውን አንድ የጨረታ ማስከበሪያ ሲ.ፒ.ኦ እና ፣ የሕጋዊነትና ቴክኒካል ሰነድ የያዘ አንድ ኦርጅናል እና፣ የሕጋዊነት፣ የቴክኒካል ሰነድ የያዘ አንድ ኮፒ በተለያየ ፖስታ እንዲሁም አንድ የፋይናንሻል ኦሪጅናል እና አንድ የፋይናንሻል ኮፒ በተለያየ የታሸገ ፖስታ በማድረግ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ አዲስ አበባ አዲሱ ገበያ አካባቢ በሚገኘው የዩኒቨርሲቲው ጉዳይ ማስፈጸሚያ ቢሮ በማቅረብ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 16ኛው ቀን በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር እስከ ጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው የሚዘጋው የጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ቀን ተከታታይ ቀን ተቆጥሮ በ16ኛው ቀን በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በዚሁ ዕለት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4፡15 ሰዓት ላይ አዲስ አበባ አዲሱ ገበያ አካባቢ በሚገኘው የዩኒቨርሲቲው ጉዳይ ማስፈጸሚያ ቢሮ ይከፈታል፡፡ 16ኛው ቀን የበዓል ቀን ከሆነ ወይም የሥራ ቀን ካልሆነ በቀጣይ የሥራ ቀን በተጠቀሰው ቦታና ሰዓት ይከፈታል፡፡ ተጫራቾች የፋይናንሻል ዶክመንት የሚጠቀሙት ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው ፎርም ላይ በመሆኑ ዋጋቸውን የሚሞሉት በዚሁ ሰነድ ላይ ይሆናል፡፡
6. ሕጋዊነት እና ቴክኒካል ግምገማ አሟልተው ያለፉ ተጫራቾች የፋይናንሽያል ጨረታ ሰነዳቸው የሚከፈተው በአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
7. አሸናፊ ተጫራቾች የውል ማሰከበሪያ ያሸነፉበትን 10% በዩኒቨርሲቲው ስም በማሠራት አሸናፊነታቸው በተገለጸላቸው በ7 ቀናት ውስጥ ውል ባይገቡ ለጨረታ ማስከበሪያነት ያስያዙት ለመንግስት ገቢ ሆኖ ዩኒቨርስቲው የራሱን አማራጭ ይወስዳል፡፡
8. ተጫራቾች በጨረታው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ባይገኙ የጨረታውን መክፈት ሂደት አያስተጓጉልም፡፡
9. ዩኒቨርሲቲው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
10. ተጫራቾች የሚያቀርቧቸውን ዕቃዎች ናሙና ጨረታው ከመከፈቱ 3 ቀናት በፊት ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን በጨረታ መክፈቻ ዕለት ናሙና የሚያቀርብ ተጫራች አይስተናገድም፡፡
11. አንድ ተጫራች ሌሎች ባቀረቡት ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይችልም፡፡
12. የጨረታ ግምገማ ውጤት በውስጥ ማስታወቂያ ይገለጻል፡፡
13. ዕቃው የሚቀርብበት ቦታ /የርክክብ ቦታ/ አሶሶ ዩኒቨርሲቲ መጋዘን ይሆናል፡፡

ስለ ጨረታው የበለጠ ማብራሪያ ካስፈለገ

በስልክ ቁጥር ፡- 0578875014/ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ**

**አሶሳ**